# የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ

## የልዩ ትምህርት እና የተማሪ አገልግሎቶች ዲቪዥን

# የቤተሰብዎ የልዩ ትምህርት መብቶች

## የቨርጂንያ የአሰራር ከለላዎች ማሳወቂያ (ፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ)

የልዩ ትምህርት የአሰራር ከለላዎች መስፈርቶች

**ሴፕተምበር 2013 ላይ የተከለሰ**

ይህ ሰነድ፣ ኦክቶበር 2012 ላይ በቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) የተጻፈውን የአሰራር ከለላዎች ሰነድ አሻሽሎ ያቀርባል። በሚከተሉት ስልጣኖች ላይ ከለሳዎቹ ይንፀባረቃሉ፡-

- *የ2004 የአካል ጉዳተኛ ግለሰቦች የትምህርት ማሻሻያ ድንጋጌ* (የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA)፤ P.L. 108-446; 20 USC § 1400 et seq.) በዲሰምበር 3፣2004 የታተመ፤ ጁላይ 1፣2005 ላይ ተፈጻሚ የሆነ፤
- የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) 34 CFR ክፍል 300 ተግባራዊ የሚያደርግ የፌደራል ደንቦች፤ ኦገስት 14፣ 2006 የታተመ፤ ኦክቶበር 13፣ 2006 ላይ ተፈጻሚ የሆነ፤
- ተጨማሪ የፌደራል የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ደንቦችን፤ 34 CFR ክፍል 300፤ በፌደራል መዝገብ Vol. 73፣ ቁጥር 231፤ በዲሰምበር 1፣ 2008 የታተመ፤ በዲሰምበር 31፣ 2008 ተፈጻሚ የሆነ፤
- ተጨማሪ የፌደራል የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ደንቦችን፤ 34 CFR ቁጥር 300፤ በፌደራል መዝገብ Vol. 78፣ ቁጥር 31፤ ፌብርዋሪ 14፣ 2013 የታተመ፤ ማርች18፣ 2013 ተፈጻሚ የሆነ፤
- *በቨርጂኒያ ውስጥ የአካል ጉዳተኛ ልጆች የልዩ ትምህርት ፕሮግራሞችን የሚቆጣጠሩ ደንቦች* (*የቨርጂኒያ ደንቦች*) 8 VAC 20-81-10 et seq፤ ጁላይ 7፣ 2009 ታትሞ ተፈጻሚ የሆነ።

ይህ ሰነድ ከዩኤስ የትምህርት መምሪያ ሞዴል የአሰራር ከለላዎች ማሳወቂያ (ጁን 2009 ላይ የተከለሰው) ይጣጣማል እና በዚህ ማሳወቂያ ውስጥ መካተት ያለባቸውን የተወሰኑ የቨርጂኒያ መስፈርቶችን ያካትታል።

ስለ የልዩ ትምህርት እና ስለእነዚህ የአሰራር ከለላዎች ተጨማሪ መረጃ የአካባቢዎን የልዩ ትምህርት ዳይሬክተር ወይም የትምህርት ቤት ርእሰ መምህርን፣ የአካባቢዎን ትምህርት ዲቪዥን፣ የወላጅ መርጃ ማዕከልን፣ የወላጅ የትምህርት ተሟጋች ማሰልጠኛ ማዕከልን (PEATC)፣ ወይም የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) የክርክር አፈታት እና አስተዳደራዊ አገልግሎቶችን ቢሮ በ 804-225-2013 በማነጋገር ማግኘት ይችላሉ።
ይህ ሰነድ በ https://www.doe.virginia.gov/home/showpublisheddocument/922 ላይም ይገኛል።

ከክፍያ ነጻ በድምፅ: 800-422-2083
ከክፍያ ነጻ TDD: 800-422-1098

# ማውጫ

**አጠቃላይ መረጃ ..... 1**
የአሰራር ከለላዎች ምንድን ናቸው? ..... 1
አጠቃላይ እይታ፡- አንዳንድ ጠቃሚ የልዩ ትምህርት ቃላቶች ምንድን ናቸው ? ..... 1
የጽሁፍ ቅድመ ማሳወቂያ ..... 2
የአፍ መፍቻ ቋንቋ ..... 3
ኤሌክትሮኒክ ደብዳቤ ..... 3
የድምጽ እና ምስል ቀረጻ ..... 3
የወላጅ ፈቃድ – ትርጓሜ ..... 4
የወላጅ ፈቃድ ..... 5

**ገለልተኛ ትምህርታዊ ግምገማዎች ..... 9**

**የመረጃ ምስጢራዊነት ..... 10**
ትርጓሜዎች ..... 11
የግል ማንነት የሚገልጹ መረጃዎች ..... 11
ማሳወቂያ ለወላጆች ..... 11
የተደራሽነት መብቶች ..... 12
የመዳረሻ መዝገብ ..... 12
ከአንድ በላይ ልጆች መዛግብት ..... 13
የመረጃ ዓይነቶች እና መገኛ ቦታዎች ዝርዝር ..... 13
ክፍያዎች ..... 13
በወላጆች ጥያቄ መሰረት መዛግብትን ማሻሻል ..... 13
ችሎት የማግኘት እድል ..... 13
የችሎት አሰራሮች ..... 14
የችሎት ውጤት ..... 14
የግል ማንነት የሚገልጹ መረጃዎችን ይፋ የማድረግ ፈቃድ ..... 14
ከለላዎች ..... 15
መረጃን ማጥፋት ..... 15

**የግጭት አፈታት አማራጮች ..... 16**

**ሽምግልና ..... 16**

**የስቴት የቅሬታ አፈታት አሰራሮች ..... 17**
የፍትህ ሂደት ችሎት እና የስቴት ቅሬታ አፈታት አሰራሮች መካከል ያለው ልዩነት ..... 17
የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) የቅሬታ አፈታት አሰራር ተግባራዊ ስለማድረግ ..... 18
አነስተኛው የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) የቅሬታ አፈታት አሰራሮች ..... 18
ቅሬታ ማቅረብ ..... 19

**የፍትህ ሂደት አሰራሮች ....... 20**
ለፍትህ ሂደት የችሎት ጥያቄ ማቅረብ ....... 20
ለፍትህ ሂደት ጥያቄ ማቅረብ ....... 21
የሞዴል ቅጾች ....... 23
የፍትህ ሂደት ችሎት በመጠባበቅ ላይ የተማሪ ምደባ ....... 23
የመፍትሄ ሂደት ....... 24
የማያዳላ የፍትህ ሂደት ችሎት ....... 26
የችሎት መብቶች ....... 27
የችሎት ውሳኔዎች ....... 28
የችሎት እና ግምገማዎች የጊዜ ሰሌዳዎች እና አመቺነት ....... 29
የፍትሐ ብሄር ክሶች እና ክሶቹ የሚመሰረቱበት የጊዜ ገደብ ....... 29
የጠበቃ ክፍያዎች ....... 30

**የአካል ጉዳተኛ ልጆችን ስነ-ምግባር ለማስጠበቅ የሚውሉ አሰራሮች ....... 31**
የትምህርት ቤት ሰራተኞች ሥልጣን ....... 32
በስነ ምግባር ጉድለት ምክንያት ስለሚደረግ የምደባ ለውጥ ....... 35
የጊዜያዊ የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታን ውሳኔ ....... 35
ይግባኝ ....... 36
በይግባኝ ወቅት ስለሚኖር ምደባ ....... 37
ለልዩ ትምህርት እና ተያያዥ ለሆኑ አገልግሎቶች ለጊዜው ብቁ ላልሆኑ ልጆች ስለሚደረግ ጥበቃ ....... 37
ጉዳዩን ለሕግ አስከባሪ እና ለፍርድ ቤት አካላት መላክ እና በእነርሱ የሚወሰዱ እርምጃዎች ....... 38

**በሕዝብ ወጪ ልጆችን በራሳቸው ውሳኔ በግል ትምህርት ቤቶች ለማስገባት ተፈጻሚነት ያላቸው መስፈርቶች ....... 38**
አጠቃላይ ....... 38

**የህዝብ ጥቅሞችን ወይም ኢንሹራንስ አጠቃቀምን በተመለከተ የወላጅ መብቶች ማሳወቂያ ....... 40**

# አጠቃላይ መረጃ[1]

## መግቢያ፡- የአሰራር ከለላዎቹ ምንድን ናቸው?

ይህ "የቤተሰብዎ የልዩ ትምህርት መብቶች" ሰነድ ከአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ትምህርት የሚመራ የፌዴራል ሕግ "የ2004 የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ" (IDEA) ቁልፍ ክፍሎችን ለይቶ ያወጣል። የ2004 የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ " (IDEA)፤ ቤተሰቦች እና ትምህርት ቤቶች ችግሮችን እንዴት መፍታት እንደሚችሉ ጨምሮ ስለ የልዩ ትምህርት መብታቸው እንዲነገራቸው ይጠይቃል። ጥያቄዎች ካልዎት ወይም ስለ የልዩ ትምህርት አሰራር የበለጠ ለማወቅ ከፈለጉ፣ እባክዎን የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) የወላጅ እንባ ጠባቂን በስልክ ቁጥር 804-371-7420፣ የአካባቢዎን የልዩ ትምህርት ዳይሬክተር፣ የአካባቢዎ የወላጅ መረጃ ማዕከል፣ ወይም የወላጅ የትምህርት ተሚጋች ማሰልጠኛ ማዕከልን በ1-800-869-6782 ወይም በኢሜይል: partners@peatc.org. ያግኙ።

## አጠቃላይ እይታ፡- አንዳንድ ጠቃሚ የልዩ ትምህርት ቃላቶች ምን ድን ናቸው?

ትምህርት ቤት ውስጥ አካል ጉዳተኛ መሆናቸውን የተለዩና ከትምህርታቸው ጥቅም ለማግኘት የልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚያስፈልጋቸው እያንዳንዱ ተማሪ ነጻ እና አግባብነት ያለው የህዝብ ትምህርት (FAPE) የማግኘት መብት እንዳለው የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ይገልጻል።

ነጻ እና አግባብነት ያለው የህዝብ ትምህርት (FAPE) በዝቅተኛው ገዳቢ የሆነ አካባቢ (LRE) መሰጠት አለበት። ይህ ማለት በተቻለ መጠን የልጁን የትምህርት ፍላጎቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ እያንዳንዱ አካል ጉዳተኛ ልጅ ክፍል ውስጥ እና በሌሎች ተግባራት ውስጥ አካል ጉዳተኛ ካልሆኑ ልጆች ጋር ይሳተፋል።

ለእያንዳንዱ ተማሪ፣ ነጻ እና አግባብነት ያለው የህዝብ ትምህርት (FAPE) እንዴት እንደሚሰጥ እቅድ በየአመቱ ይዘጋጃል። ይህ እቅድ የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) በመባል ይታወቃል። የተናጠል የትምህርት ፕሮግራሞች (IEPs) የሚዘጋጁት ወላጅ (ጆች)ን ባካተተ በልጁ የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን ነው። ወላጆች "የፈቃድ መብቶች" አሏቸው፣ ይህም ማለት ትምህርት ቤቱ እርምጃ ከመውሰዱ በፊት አንዳንድ ድርጊቶችን ወላጆች ማጽደቅ አለባቸው። ቤተሰቦች፣ ልጆቻቸው የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ግቦቻቸውን ላይ ለመድረስ ስላደረጉት የእድገት መደበኛ ሪፖርቶችን ማግኘት አለባቸው።

የተናጠል የትምህርት ፕሮግራሞች (IEPs) በከፊል የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- አሁን ላይ ያለው የአካዳሚክ ስኬት እና የተግባር አፈጻጸም ደረጃ፣
- የሚቀርቡት ልዩ እርዳታዎች እና አገልግሎቶች መግለጫ፣
- በሚለኩ ቃላት የተገለጹ አመታዊ ግቦች፣
- ተማሪው በመደበኛ ትምህርት ክፍል የማይሳተፍባቸውን ሰዓታት ማብራሪያ፣
- ለክፍሎች እና ፈተና አስፈላጊ የሆኑ መስተንግዶዎች ዝርዝር እና
- የመማሪያ ደረጃዎች (SOL) ፈተናዎችን ጨምሮ ተማሪው በስቴቱ የተጠያቂነት ስርዓት ውስጥ እንዴት እንደሚሳተፍ የሚገልጽ እቅድ።

[1] በዚህ ሰነድ ውስጥ ያሉትን ድንጋጌዎች የሚሸፍነው የአካል ጉዳተኞች ትምህርት ማሻሻያ ድንጋጌ (IDEA) ክፍል B በመባል ይታወቃል። ከዚህ በኋላ በዚህ ሰነድ ውስጥ፣ ግልጽ ለማድረግ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር የአካል ጉዳተኞች ትምህርት ማሻሻያ ድንጋጌ (IDEA) ፣ ያለ መለያ ክፍሉ የአካል ጉዳተኞች ትምህርት ማሻሻያ ድንጋጌ (IDEA) ተብሎ የሚጻፍ ይሆናል። የልዩ ትምህርትን የሚቆጣጠሩ የቨርጂኒያ ደንቦች በዚህ ሰነድ ውስጥ የቨርጂኒያ ደንቦች ተብለው ይጻፋሉ።

## የጽሁፍ ቅድመ ማሳወቂያ

**የልጅዎን የትምህርት ፍላጎቶች ስለሚያካትቱ የትምህርት ዲቪዥኑ ድርጊቶች በጽሁፍ መረጃ የማግኘት መብት አልዎት። መረጃው ለትምህርታዊ ውሳኔዎች በመረጃ ላይ የተመሰረተ ፈቃድ እንዲሰጡ ይረዳዎታል።**

### ማሳወቂያ

የትምህርት ዲቪዥኑ የሚከተሉትን ለማድረግ የጽሁፍ ማሳወቂያ ሊሰጥዎ ይገባል (በጽሁፍ የተወሰነ መረጃ ይሰጥዎታል) ፡-

1. የልጅዎን መለያ፣ ግምገማ ወይም የትምህርት ምደባ፣ ወይም ለልጅዎ ነጻ እና ተገቢ የሆነ የህዝብ ትምህርት (FAPE) አቅርቦት እንዲሰጠው ወይም እንዲለወጥለት ሐሳብ ማቅረብ፤ **ወይም**
2. የልጅዎን መለያ፣ ግምገማ ወይም ትምህርታዊ ምደባ፣ ወይም ለልጅዎ የነጻ እና ተገቢ የሆነ የህዝብ ትምህርት (FAPE) አቅርቦትን ለመጀመር ወይም ለመለወጥ ፈቃደኛ አለመሆን።

### የማሳወቂያ ይዘት

የጽሁፍ ማሳወቂያው የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

1. የትምህርት ዲቪዥንዎ ያቀረበውን ወይም ለማድረግ ፈቃደኛ ያልሆነውን እርምጃ መግለጫ፤
2. የትምህርት ዲቪዥንዎ ለምን እርምጃ እንደሚወስድ ወይም መውሰድ እንደማይፈልግ ማብራሪያ፤
3. የትምህርት ዲቪዥንዎ ድርጊቱን ለማቅረብ ወይም ላለማቅረብ ሲወስን ጥቅም ላይ የዋለውን እያንዳንዱን የግምገማ ሂደት፣ ምዘና፣ መዝገብ፣ ወይም ሪፖርት ማብራሪያ፤
4. በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ስር ባለው የአሰራር ከለላዎች ድንጋጌዎች ውስጥ ጥበቃዎች እንዳሉዎት የሚገልጽ መረጃ፤
5. የትምህርት ዲቪዥንዎ ያቀረበው ወይም የሚከለክለው እርምጃ ለግምገማ የመጀመሪያ ሪፈራል ካልሆነ፣ የአሰራር ከለላዎች መግለጫ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ የሚያስችል መረጃ፣
6. የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌን (IDEA) ለመረዳት እርዳታ የሚያገኙባቸው የመገኛ ምንጮች፣
7. የልጅዎ የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን ያገናዘበባቸውን ሌሎች ምርጫዎች እና ምርጫዎቹ ውድቅ የተደረጉበትን ምክንያቶች ማብራሪያ፣ **እና**
8. የትምህርት ዲቪዥንዎ ድርጊቱን ለምን እንዳቀረበ ወይም እንዳልተቀበለ ሌሎች ምክንያቶች መግለጫ።

### በሚረዱት ቋንቋ ማሳወቂያ

ማሳወቂያው፡-

1. በሰፊው ህዝብ በሚረዱት ቋንቋ የተጻፈ፤ **እና**
2. ተግባራዊ ሊደረግ የማይቻል ካልሆነ በስተቀር፣ በአፍ መፍቻ ቋንቋዎ ወይም በሌላ የመግባቢያ ዘዴ የቀረበ መሆን አለበት።

የአፍ መፍቻ ቋንቋዎ ወይም ሌላ የመግባቢያ ዘዴዎ የጽሁፍ ቋንቋ ካልሆነ፣ የትምህርት ዲቪዥንዎ፡-

1. ማሳወቂያው በአፍ መፍቻ ቋንቋዎ ወይም በሌላ የመገናኛ ዘዴ ለእርስዎ በቃል እንዲተረጎምልዎት ማድረግ፤
2. የማሳወያው ይዘት መረዳትዎን፤ እና
3. ቁጥር 1 እና 2 መሟላታቸውን የሚያሳይ የጽሁፍ ማስረጃ መኖሩን ማረጋገጥ አለበት።

**የአፍ መፍቻ ቋንቋ**

---

**በሚረዱት ቋንቋ መረጃ የማግኘት መብት አልዎት።**

*የአፍ መፍቻ ቋንቋ፣* የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታው ከተገደበ ግለሰብ በተመለከተ ጥቅም ላይ ሲውል የሚከተለው ማለት ነው፡-

1. ያ ሰው በተለምዶ የሚጠቀምበት ቋንቋ፣ ወይም ልጅ ከሆነ፣ የልጁ ወላጆች በመደበኛነት የሚጠቀሙበት ቋንቋ፤
2. ከልጆች ጋር በቀጥታ በሚገናኙበት ጊዜ (የልጁን ግምገማን ጨምሮ) ልጁ በቤት ውስጥ ወይም በትምህርት ቤት አካባቢ የሚጠቀምበት ቋንቋ።

መስማት ለተሳነው ወይም ለዓይነ ስውር፣ ወይም የጽሑፍ ቋንቋ እውቀት ለሌለው ሰው፣ የመገናኛ ዘዴው ግለሰቡ በተለምዶ የሚጠቀመው (እንደ የምልክት ቋንቋ፣ ብሬይል ወይም የቃል ተግባቦት) ይሆናል።

**ኤሌክትሮኒክ ደብዳቤ**

---

**በትምህርት ድቪዥንዎ እንደ ምርጫ ከቀረበልዎት፣ በኢሜይል መረጃ ለማግኘት የመምረጥ መብት አልዎት።**

የትምህርት ዲቪዥንዎ ለወላጆች ሰነዶችን በኢሜይል እንዲደርሳቸው የሚያስችል ምርጫ ከሰጠ፣ የሚከተሉትን በኢሜይል እንዲደርስዎት መምረጥ ይችላሉ፤

1. የቅድሚያ የጽሁፍ ማሳወቂያ፤
2. የአሰራር ከለላዎች ማሳወቂያ እና
3. ከፍትህ ሂደት ጥያቄ ጋር የተያያዙ ማሳወቂያዎች።

**የድምጽ እና ምስል ቀረጻ**

---

**የልጅዎን ብቁነት፣የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) እና/ወይም የስነ ምግባር ማጣራት ጉዳዮችን የሚያካትቱ ስብሰባዎችን በድምጽ የመቅረጽ መብት አልዎት።**

የልዩ ትምህርትን የሚቆጣጠሩት የፌደራል ህግ እና ደንቦች ወላጆች ከልጆቻቸው የልዩ ትምህርት ፕሮግራም ጋር የተያያዙ ስብሰባዎችን በድምጽ ወይም በምስል የመቅረጽ ደንቦቹን የመወሰን ለስቴቶች ሰጥታቸዋል። የቨርጂኒያ የልዩ ትምህርት ደንቦች እነዚህን መስፈርቶች የሚገልጹ በአሰራር ከለላዎች ስር ያሉ ድንጋጌዎችን ያካትታሉ።

የልጅዎን ብቁነት፣የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) እና/ወይም የስነ ምግባር ማጣራት ጉዳዮችን የሚያካትቱ ስብሰባዎችን በድምጽ መቅረጽ ይችላሉ።

- ስብሰባውን በድምጽ እንደቀርጹ ከስብሰባው በፊት ለትምህርት ቤትዎ ሰራተኞች በጽሁፍ ማሳወቅ አለብዎት። ይህንን ድርጊት ለትምህርት ቤት ሰራተኞች አስቀድመው ካላሳወቁ የድምጽ ቀረጻውን ቅጂ መስጠት አለብዎት።
- ለድምጽ ቀረጻው የሚጠቀሙበት የድምጽ መሳሪያዎች እና ቁሳቁሶች ሃላፊነቱ የሚወስዱት እርስዎ ነዎት።
- የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች በድምጽ ስብሰባውን ከቀረጹ ወይም የድምጽ ቀረጽውን ቅጂ ከተቀበሉ፣ የድምጽ ቅጂው የልጅዎ የትምህርት መዝገብ አካል ሆኖ ይቀመጣል።

የትምህርት ዲቪዥኑ የሚከተሉትን እንዳይጠቀሙ የሚከለክል፣ የሚገድብ ወይም በሌላ መንገድ የሚቆጣጠሩ ፖሊስዎች ሊኖሩት ይችላል፤

- በስብሰባዎች የምስል ቀረጻ መሳሪያዎች፤ ወይም
- እላይ ከተገለጹት ስብሰባዎች ውጭ በስብሰባዎች ላይ የድምጽ ወይም የምስል ቀረጻ መሳሪያዎች።

የትምህርት ዲቪዥን ፖሊሲዎች፡-

- ቅጂዎቹ የልጁ የትምህርት መዝገብ አካል እንዲሆኑ መደንገግ፤
- ፖሊሲው ወጥ በሆነ መልኩ መተግበሩን ማረጋገጥ አለባቸው።

ፖሊሲው መሳሪያዎቹ መጠቀምን የሚከለክል ከሆነ፣ በልዩ ትምህርት በሚመሩ ህጎች እና መመሪያዎች ስር ወላጅ የተናጠል የትምህርት ፕሮግራምን (IEP)፣ የልዩ ትምህርት ሂደትን ወይም ሌሎች የወላጅ መብቶችን በመተግበር ላይ አስፈላጊ ከሆነ ከተለመዱ ውጪ ልዩ ሁኔታዎችን ማቅረብ አለበት።

## የወላጅ ፈቃድ – ትርጓሜ

**መረጃ ከሌላ ጋር እንዲጋራ ወይም የተወሰኑ እርምጃዎች እንዲወሰዱ የመፍቀድ መብት አልዎት፣ እና ስለመብቱ በሚረዱት ቋንቋ ሊነገሩዎት ይገባል። ፈቃድዎትን መልሶ የመውሰድ (የመሻር) መብት አልዎት።**

### ፈቃድ

*ፈቃድ ማለት፡-*

1. ፈቃድ ስለሚሰጡበት ድርጊት ሁሉንም መረጃ በአፍ መፍቻ ቋንቋዎት ወይም በሌላ የመገናኛ ዘዴ (እንደ የምልክት ቋንቋ፣ ብሬይል ወይም የቃል ተግባቦት ያሉ) ሙሉ በሙሉ ተነግረዎታል።
2. ድርጊቱን መረዳትዎንና በጽሁፍ ስምምነትዎን ገልጸዋል እና ፈቃዱ ያንን ድርጊት ይገልጻል፤ መዝገቦቹን (ካሉ) እና ለማን እንደሚለቀቁትም ይዘረዝራል፤ **እና**
3. ፈቃዱ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ እንደሆነ እናም በማንኛውም ጊዜ ስምምነትዎን ማንሳት እንደሚችሉ ተረድተዋል። የስምምነትዎ መሻር ስምምነትዎን ከሰጡ በኋላ እና ከመሻር በፊት የተከሰተውን ድርጊት አይሽረውም (አይቀለብሰውም)።

**የተወሰኑ የፈቃድ መብቶች አልዎት። ለምሳሌ፣ ትምህርት ቤቱ ልጅዎን ለልዩ ትምህርት ለመገምገም፣ እና ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን መስጠት ለመጀመር፣ ለመለወጥ ወይም ለማቆም የእርስዎን ፈቃድ ማግኘት አለበት።**

***ለመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ ፈቃድ***

የትምህርት ዲብሽሮንዎ የሚከተሉትን ነገሮች ሳያደርግ በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ስር ልጅዎ የልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለማግኘት ብቁ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለማረጋገጥ የልጅዎን የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ ማካሄድ አይችልም።

1. ስለታቀደው ድርጊት አስቀድሞ የጽሁፍ ማሳወቂያ ለእርስዎ ሳይሰጥ፤እና
2. የእርስዎን ፈቃድ ሳያገኝ

ልጅዎ አካል ጉዳተኛ ስለመሆኑ ለመወሰን የትምህርት ዲብሽሮንዎ ለመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ መረጃ ላይ የተደገፈ የእርስዎን ፈቃድ ለማግኘት ምክንያታዊ ጥረት ማድረግ አለበት።

*የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ ፈቃድ ሰጡ ማለት ለልጅዎ ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን መስጠት እንዲጀምር ለትምህርት ድዲቪዥኑ ፈቃድዎን ሰጥተዋል ማለት አይደለም።*

ልጅዎ በሕዝብ ትምህርት ቤት የተመዘገበ ከሆነ ወይም በሕዝብ ትምህርት ቤት ለማስመዝገብ በሂደት ላይ ካሉ እና ስምምነትን ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆኑ ወይም ለመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ ፈቃድ እንዲሰጡ ለቀረበው ጥያቄ ምላሽ ካልሰጡ፣ የትምህርት ዲቪዥንዎ ግዴታ ባይሆንም በዚህ ሰነድ ውስጥ የተገለጹትን የሽምግልና ወይም የፍትህ ሂደቶች በመጠቀም የልጅዎን የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ ማካሄድ ይችላል። የትምህርት ዲቪዥንዎ በእነዚህ ሁኔታዎች የልጅዎን ግምገማ ካላካሄደ ልጅዎን የማግኘት፣ የመለየት እና የመገምገም ግዴታዎቹን አይጥስም።

**በስቴት አሳዳጊነት ስር ላሉ ልጆች የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ ልዩ ደንቦች**

[አንድ ልጅ በስቴቱ አሳዳጊነት ስር ከሆነ እና ከወላጁ ጋር የማይኖር ከሆነ]

እነዚህ ሁኔታዎች እውነት ከሆኑ፣የትምህርት ዲቪዥኑ ልጁ አካል ጉዳተኛ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለመወሰን ከወላጆች ፈቃድ አያስፈልገውም፡-

1. ምክንያታዊ ጥረቶች ቢደረጉም፣ የትምህርት ዲቪዥኑ የልጁን ወላጅ ማግኘት ሳይችል ቢቀር፣
2. የወላጆች መብቶች በስቴት ህግ መሰረት ቢቋረጥ፣ ***<u>ወይም</u>***
3. ዳኛ ትምህርታዊ ውሳኔዎችን የመስጠት እና የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ ለማድረግ ከወላጅ ውጭ ለሌላ ግለሰብ የመፍቀድ መብት ከሰጠ።

*በስቴት አሳዳጊነት ስር ያለ [የስቴቱ ዋርድ] ፣ በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ውስጥ ጥቅም ላይ እንደዋለ፣ ልጁ በሚኖርበት ስቴት የሚወሰነው የሚከተሉትን ሆኖ ሲገኝ ነው፡-*

1. የማደጎ ልጅ፣
2. በስቴቱ ህግ መሰረት በስቴት አሳዳጊነት ስር ያለ ልጅ ተደርጎ ከተወሰነ፣ ***<u>ወይም</u>***
3. በሕዝብ የልጆች ዌልፌር ኤጀንሲ ስር ከሆነ

*በስቴት አሳዳጊነት ስር ያለ [የስቴቱ ዋርድ]፣* አሳዳጊ ወላጅ ያለው የማደጎ ልጅን አያካትትም።

**አገልግሎቶች ለማግኘት የወላጅ ፈቃድ**

ለልጅዎ የልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለመጀመሪያ ጊዜ ከመስጠቱ በፊት፣ የትምህርት ዲቪዥኑ የእርስዎን በመረጃ የተደገፈ ፈቃድ ለማግኘት ምክንያታዊ ጥረት ማድረግ አለበት።

ልጅዎ ለመጀመሪያ ጊዜ የልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን እንዲያገኝ ፈቃድዎን እንዲሰጡ ለቀረበው ጥያቄ ምላሽ ካልሰጡ፣ ወይም ይህን ፈቃድ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆኑ፣ የትምህርት ዲቪዥንዎ፣ የሽምግልና እና የፍትህ ሂደት አካሄዶችን ማለትም ያለእርስዎ ፈቃድ ለልጅዎ የልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች (በልጅዎ የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን የተመከረ) እንዲሰጡ የሚያስቻለቸውን ፈቃድ ወይም ውሳኔ <u>ላይጠቀም ይችላል።</u>

ልጅዎ ለመጀመሪያ ጊዜ የልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን እንዲያገኝ ፈቃድዎን ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆኑ ወይም ይህን ፈቃድ እንዲሰጡ ለተጠየቁት ጥያቄ ምላሽ ካልሰጡ እና የትምህርት ዲቪዥኑ ለልጅዎ ፈቃድዎትን የጠየቀባቸው አገልግሎቶች የልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ካልሰጠ፣ የትምህርት ዲቪዥኑዎ፡-

1. እነዚያን አገልግሎቶች ለልጅዎ ባለመስጠቱ ምክንያት ከክፍያ ነጻ እና ተገቢ የህዝብ ትምህርት (FAPE) የተቀመጠውን መስፈርት እንዲያገኝ ለማድረግ የሚጥስ አይደለም፤ <u>**እና**</u>
2. ለልጅዎ የተነናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ስብሰባ ማድረግ ወይም የተናጠል የትምህርት ፕሮግራምን (IEP) ማዘጋጀት ፈቃድ እንዲሰጡባቸው ለተጠየቁበት የልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች አስፈላጊ አይደሉም።

**ለድጋሚ ግምገማዎች የወላጅ ፈቃድ**

የሚከተሉትን ማስረጃዎችን ካላቀረበ በስተቀር፣ ልጅዎን እንደገና ከመገምገሙ በፊት፣ የትምህርት ዲቪዥንዎ በመረጃ ላይ የተመሰረተ የእርስዎ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡-

1. ለልጅዎ ግምገማ የእርስዎን ፈቃድ ለማግኘት ምክንያታዊ እርምጃዎችን ወስዷል፤ <u>**እና**</u>
2. እርስዎ ምላሽ አልሰጡም።

እንደዛ ከሆነ፣ የትምህርት ዲቪዥኑ የድጋሚ ግምገማው ሂደቱ ይቀጥላል።

ለልጅዎ የድጋሚ ግምገማ ፈቃደኛ ካልሆኑ፣ የትምህርት ዲቪዥኑ የልጅዎን ግምገማ ለመከታተል፣ግዴታ ባይሆንም፣ የሽምግልና እና የፍትህ ሂደት አካሄዶችን በመጠቀም የልጅዎን ድጋሚ ግምገማ ላለማድረግ ውሳኔዎትን ሊሽር ይችላል። እንደ የመጀመሪያም ደረጃ ግምገማዎች፣ የትምህርት ዲቪዥንዎ በዚህ መንገድ ግምገማውን ለመከታተል ፈቃደኛ ካልሆነ በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ስር ያሉትን ግዴታዎች እየጣሰ አይደለም።

**የወላጆችን ፈቃድ ለማግኘት የተደረጉ ምክንያታዊ ጥረቶች የሚያሳዩ ሰነዶች**

የትምህርት ቤት ዲቪዥንዎ ለመጀመሪያ ደረጃ ግምገማዎች የወላጅ ፈቃድ ለማግኘት፣ ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለመጀመሪያ ጊዜ ለመስጠት፣ እንደገና ለመገምገም እና በስቴት አሳዳጊነት ስር ያሉ ልጆች ወላጆችን ለመጀመሪያ ደረጃ ግምገማዎች ለማግኘት ምክንያታዊ ጥረቶች ማድረጉን ለማሳየት ሰነዶችን መያዝ አለበት። ሰነዱ የትምህርት ዲቪዥኑ በነዚህ ጉዳዮች ረገድ ያደረጋቸውን የሙከራዎች መዝገብ ማካተት አለበት። ለምሳሌ፡-

1. የተደረጉ ወይም የተሞከሩ የስልክ ጥሪዎች ዝርዝር መዝገቦች እና የጥሪዎቹ ውጤቶች፣
2. ለወላጆች የተላኩ የደብዳቤ ቅጂዎች እና የተቀበሉት ምላሾች፣ <u>**እና**</u>
3. ወደ ወላጅ ቤት ወይም የስራ ቦታ የተደረጉ ጉብኝቶች ዝርዝር መዝገቦች እና የእነዚያ ጉብኝቶች ውጤቶች።

***ፈቃድዎን መሻር***

ልጅዎ በማንኛውም ጊዜ የልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ማግኘቱን እንዳይቀጥል ፈቃድዎን የመሻር መብት አለዎት። እንደዚህ አይነት የፈቃድ መሻር ውሳኔዎች ልጅዎ እያገኛቸው ባሉት ሁሉም የልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። ስለ አንድ የተወሰነ አገልግሎት ካልተስማሙ፣ ይህንን ችግር ከልጅዎ የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን ጋር ተነጋግረው መፍታት ይችላሉ፤ ችግሩ ካልተፈታ፣ ጉዳዩን ለመፍታት ሽምግልና እና የፍትህ ሂደት መጠቀም ሌላ አማራጮች ናቸው።

- ይህንን ጥያቄ ለአካባቢዎ የልዩ ትምህርት ዳይሬክተር፣ ለልጅዎ ርእሰ መምህር፣ ወይም ለልጅዎ የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) አስተባባሪ በጽሁፍ ማቅረብ አለብዎት።

- ለልጅዎ የሚሰጠውን አገልግሎት ከማቋረጡ በፊት የትምህርት ዲቪዥንዎ የቅድሚያ ማሳወቂያ በጽሁፍ ሊሰጥዎ ይገባል።

- ሃሳብዎን ለማስቀየር ወይም የችሎት ሹሙን በውሳኔዎ ላይ ብይን ለመስጠት፣ የትምህርት ዲቪዥንዎ ሽምግልና ወይም የፍትህ ሂደት ላይጠቀም ይችላል።

- የትምህርት ዲቪዥንዎ ለልጅዎ አገልግሎቶቹ እንዲቆሙ የጠየቁበትን ምክንያት እንዲያብራሩ ላያስገድድዎት ይችላል።

- በኋላ ሀሳብዎን ከቀየሩ እና ልጅዎ እንደገና አገልግሎት እንዲያገኝ ከፈለጉ፣የትምህርት ዲቪዥንዎ ጥያቄዎን እንደ ድጋሚ ግምገማ ሳይሆን እንደ የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ ጥያቄ አድርጎ መቁጠር አለበት።

የእርስዎ ፈቃድ መሻር ተግባራዊ ከሆነ በኋላ፣ እባክዎን እነዚህ ነገሮችን ያስታውሱ፦

- ልጅዎ እንደማንኛውም አካል ጉዳተኛ ያልሆኑ ተማሪዎች፣ አካል ጉዳተኛ ላልሆኑ ተማሪዎች የሚሰጡት መስተንግዶዎችን (ካሉ) ጨምሮ፣ እኩል ይስተናገዳሉ።

- የልጅዎ የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ከዛ በኋላ አይሰራም።

- ልጅዎ አካል ጉዳተኛ ላልሆኑ ተማሪዎች የስነ ምግባር ህጎች ተገዢ ይሆናል።

- ልጅዎ በተሻሻለው የዲፕሎማ ትራክ ላይ ከነበረ፣ ከአሁን በኋላ ለዚህ የዲፕሎማ ምርጫ ብቁ አይሆንም። ልጅዎ ዲፕሎማ ለማግኘት የመደበኛ ዲፕሎማውን ሁሉንም መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል።

***ሌሎች የፈቃድ መስፈርቶች***

በቨርጂንያ ውስጥ፣ የሚከተሉትን ከመደረጋቸው በፊት የእርስዎ ፈቃድ ያስፈልጋል።

- በልጅዎ የአካል ጉዳተኛነት መለያ እና በልጅዎ የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ላይ ለሚደረጉ ማናቸውም ለውጦች፤

- ለልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች በልጅዎ ብቁነት ላይ የተደረጉ ማናቸውም ለውጦች፤ እና

- ልጅዎ በመደበኛ ወይም በአድቫንስ ስታዲስ ዲፕሎማ ካልተመረቀ በስተቀር፣ ማንኛውም ከፊል ወይም ሙሉ የልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች መቋረጥ።

የትምህርት ዲቪዥኑ የሚከተሉትን ከማድረጉ በፊት የእርስዎ ፈቃድ አያስፈልገውም፡-

1. ነባር መረጃዎችን እንደ የልጅዎ የግምገማ አካል መገምገም ወይም የድጋሚ ግምገማ ለማካሄድ፤ **ወይም**
2. ከፈተና ወይም ግምገማ በፊት፣ ከሁሉም ልጆች ወላጆች ፈቃድ ካልተፈለገ በስተቀር፣ለሁሉም ልጆች የሚሰጠውን ፈተና ወይም ሌላ ግምገማ ለልጅዎ ለመስጠት።

የትምህርት ዲቪዥንዎ ለአንድ አገልግሎት ወይም እንቅስቃሴ የእርስዎን ፈቃደኛ አለመሆንዎን፣ እርስዎ ወይም ልጅዎን ለሌላ ማንኛውንም አገልግሎት፣ ጥቅም ወይም እንቅስቃሴ ለመከልከል ላይጠቀምበት ይችላል።

ልጅዎን በራስዎ ወጪ በግል ትምህርት ቤት ውስጥ ካስመዘገቡት ወይም ልጅዎን በቤት ውስጥ የሚያስተምሩ ከሆነ፣ እና ለልጅዎ የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ ወይም የልጅዎ ድጋሚ ግምገማ ፈቃድዎን ካልሰጡ፣ ወይም ፈቃድዎን ለመስጠት ለቀረበው ጥያቄ ምላሽ ሳይሰጡ ቢቀሩ፣ የትምህርት ዲቪዥንዎ ፈቃድዎትን የመሻር ሂደቶችን (ማለትም፣ ሽምግልና እና የፍትህ ሂደት አካሄዶች) ላይጠቀም ይችላል እና ልጅዎን ፍትሃዊ አገልግሎቶችን ለማግኘት ብቁ አድርጎ እንዲቆጥር አይገደድም (በወላጆች ፍላጎት በግል ትምህርት ቤት ውስጥ ለሚማሩ የአካል ጉዳተኛ ልጆች የሚሰጡ አገልግሎቶች)።

### ፈቃድ - አሳዳጊ ወላጆችን በተመለከተ ልዩ መስፈርት

ልጅዎ ከአሳዳጊ ወላጅ ጋር የሚኖር ከሆነ እና የወላጅ መብቶችዎ ካልተቋረጡ፣ የትምህርት ዲቪዥንዎ፣ የትምህርት ቤት ሰራተኞች የልጅዎን የልዩ ትምህርት ፕሮግራም በተመለከተ ውሳኔ እንዲያደርጉ በአሳዳጊ ወላጅ ላይ እንደሚሞረከዙ የጽሁፍ ማሳወቂያ መላክ አለበት። እነዚህ ውሳኔዎች የልጅዎን የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) አገልግሎቶች እና ምደባ፣ እንዲሁም የብቁነት ውሳኔዎችን ከሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ይገናኛሉ።

በትምህርት አመቱ መጀመሪያ ላይ ወይም በማንኛውም የትምህርት አመት በማንኛውም ጊዜ ከልጅዎ የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ጋር የተያያዘ ስብሰባ ወይም ለልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ብቁነት ግምገማ ሲኖር የትምህርት ዲቪዥኑ ይህንን የጽሁፍ ማሳሰቢያ ይልክልዎታል። የልጅዎ ልዩ ትምህርት ፕሮግራምን በሚመለከቱ ጉዳዮች እንደ የልጅዎ ባዮሎጂካል ወላጅ ወይም የጉዲፈቻ ወላጅ ምላሽ እንደሚሰጡ ለትምህርት ዲቪዥኑ እስኪያሳወቁ ድረስ የትምህርት ዲቪዥኑ ማሳወቂያ ተፈጻሚ ይሆናል። የትምህርት ዲቪዥኑ የአሁኑ ፖስታ እና የመገኛ አድራሻዎ እንዳለው ያረጋግጡ።

### የተዘዋወሩ ተማሪዎች - ወደ ሌላ ቦታ ቢዘዋወሩ ምን ይከሰታል?

ቤተሰብዎ በቨርጂኒያ ውስጥ ወደሚገኝ ሌላ የትምህርት ዲቪዥን ከተዛወሩ ወይም ከሌላ ስቴት ወደ ቨርጂኒያ ከተዛወሩ፣ አዲሱ የትምህርት ዲቪዥን የልጅዎን የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) በአዲሱ ትምህርት ቤት ወዲያውኑ ተግባራዊ ለማድረግ የእርስዎን ፈቃድ አያስፈልገውም። ሆኖም፣ አዲሱ የትምህርት ዲቪዥን፣ ከእርስዎ ጋር በመመካከር፣ ልጅዎ የልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች እንደሚያገኝ እና በልጅዎ የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ውስጥ ከተገለጹት ጋር የሚነጻጸር አገልግሎቶችን ማካተቱን ማረጋገጥ አለበት።

- አዲሱ የትምህርት ዲቪዥን የቀድሞ የትምህርት ዲቪዎን በማነጋገር ከልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች አቅርቦት አንጻር የልጅዎን መዝገብ ለማግኘት የተቻለውን ሁሉ ጥረት ያደርጋል። አዲሱ የትምህርት ቤት ዲቪዥን ከሚከተሉት አማራጮች አንዱን ይወስናል፡-

  ✔ በእርስዎ ፈቃድ፣ ያለፈውን የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) መቀበል እና መተግበር፤
  ወይም

- ✔ በእርስዎ ፈቃድ፣ አዲስ የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ለማዳበር የሚያስፈልግ ማንኛውንም መረጃ እያገኙ እና እየገመገሙ፣ ጊዜያዊ IEP ማዳበር እና መተግበር፣ወይም
- ✔ በእርስዎ ፈቃድ፣ ግምገማ በማካሄድ፣ አዲስ የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ማዘጋጀት እና መተግበር።

- እርስዎ እና የትምህርት ቤት ሰራተኞች በጊዜያዊ አገልግሎቶች ወይም በአዲስ የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ላይ መስማማት ካልቻላችሁ፣ እርስዎ እና/ወይም አዲሱ የትምህርት ዲቪዥን አለመግባባቱን ለመፍታት የግጭት አፈታት አማራጮችን የሽምግልና ወይም የፍትህ ሂደትን መጀመር ትችላላችሁ። አለመግባባቱ በሚፈታበት ጊዜ፣ አዲሱ የትምህርት ዲቪዥን፣ ከእርስዎ ጋር በመመካከር፣ ካለፈው የትምህርት ዲቪዥን በልጅዎ የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ውስጥ ከተገለጹት ጋር የሚመሳሰሉ አገልግሎቶችን ጨምሮ ነጻ እና ተገቢ የሆነ የሕዝብ ትምህርትን (FAPE) ማቅረብ አለበት።

# ገለልተኛ ትምህርታዊ ግምገማዎች

**በትምህርት ዲቪዥኑ በተጠናቀቀው ግምገማ ካልተስማሙ፣ በትምህርት ዲቪዥኑ ወጪ፣ ከልጅዎ የትምህርት ዲቪዥን ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች ልጅዎ እንዲገመገም የማድረግ መብት አልዎት።**

**አጠቃላይ**

ከዚህ በታች እንደተገለጸው፣ በትምህርት ዲቪዥን በተገኘው የልጅዎ ግምገማ ካልተስማሙ፣ ልጅዎን ገለልተኛ የሆነ ትምህርታዊ ግምገማ (IEE) የማግኘት መብት አለዎት።

ገለልተኛ የሆነ የትምህርታዊ ግምገማ ከጠየቁ፣ ገለልተኛ ትምህርታዊ ግምገማ የት እንደምታገኙ እና ስለ ገለልተኛ የትምህርት ግምገማ የሚመለከቱትን መመዘኛዎች መረጃ የትምህርት ዲቪዥኑ መስጠት አለበት።

**ትርጓሜዎች**

*ገለልተኛ ትምህርታዊ ግምገማ* ማለት በልጅዎ ትምህርት ዲቪዥን ውስጥ ተቀጥሮ በማይሰራ እና ኃላፊነት ባለው ፈታኝ የሚደረግ ግምገማ ነው።

*የህዝብ ወጪ* ማለት የትምህርት ዲቪዥን የግምገማውን ሙሉ ወጪ ይከፍላል ወይም ከአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ጋር በሚስማማ መልኩ ግምገማው ያለ ምንም ወጪ ለእርስዎ መሰጠቱን ያረጋግጣል፤ ይህም እያንዳንዱ ስቴት የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) መስፈርቶችን ለማሟላት በየስቴቱ የሚገኙትን የትኛውንም የስቴት፣ አካባቢያዊ፣ ፌዴራል እና የግል የድጋፍ ምንጮች እንዲጠቀም ያስችለዋል።

**በህዝብ ወጪ የሚደረግ ግምገማ የወላጅ መብት**

በሚከተሉት ሁኔታዎች ተገዢ በሚሆን እና በልጅዎ የትምህርት ዲቪዥን ባደረገው ግምገማ ካልተስማሙ፣ በሕዝብ ወጪ ለልጅዎ ገለልተኛ የሆነ ትምህርታዊ ግምገማ የማግኘት መብት አለዎት።

1. በህዝብ ወጪ የልጅዎን ገለልተኛ የሆነ ትምህርታዊ ግምገማ ከጠየቁ፣ የትምህርት ዲቪዥንዎ ያለአላስፈላጊ መዘግየት፣ ወይ (ሀ) የልጅዎ ግምገማ ተገቢ መሆኑን ለማሳየት በፍትህ ሂደት እንዲታይ የችሎት ጥያቄ ማቅረብ አለበት ወይም (ለ)እርስዎ ያገኙትን የልጅዎ ግምገማ የትምህርት ዲቪዥኑ መመዘኛዎችን እንደማያሟላ በችሎት ላይ የትምህርት ዲቪዥኑ ካላሳየ በስተቀር፣ በህዝብ ወጪ የሚደረግ ገለልተኛ የሆነ ትምህርታዊ ግምገማ ያቀርባል።

2. የትምህርት ዲቪዥንው ችሎት ከጠየቀ እና የመጨረሻው ውሳኔ የትምህርት ቤትዎ ዲቪዥን ለልጅዎ ያደርገው ግምገማ ተገቢ ነው የሚል ከሆነ፣ በህዝብ ወጪ ባይሆንም፣ አሁንም ገለልተኛ የሆነ ትምህርታዊ ግምገማ የማግኘት መብት አለዎት።

3. ለልጅዎ ገለልተኛ የሆነ ትምህርታዊ ግምገማ ከጠየቁ፣ የትምህርት ዲቪዥን ከትምህርት ቤትዎ ዲቪዥን የተገኘውን የልጅዎን ግምገማ ለምን እንደተቃወሙ ሊጠይቅ ይችላል። ነገር ግን የትምህርት ዲቪዥኑ በልጅዎ ላይ ያደርገውን ግምገማ ለመከላከል፣ማብራሪያ እንደ ግዴታ ሊጠይቅ እና ለልጅዎ በህዝብ ወጪ የሚደረግ ገለተኛ የሆነ ትምህርታዊ ግምገማ ለማቅረብ ወይም የፍትህ ሂደት ጥያቄ ለማቅረብ ያለምክንያት ማዘግየት አይችለም።

የትምህርት ዲቭዥንዎ እርስዎ የማይስማሙበት የልጅዎን ግምገማ ባደረገ ቁጥር፣ ለልጅዎ በህዝብ ወጪ የሚደረግ አንድ ገለልተኛ የሆነ የትምህርታዊ ግምገማ ብቻ እንዲያደርጉ ይፈቀድለትዋል።

**በወላጆች ተነሳሽነት ለሚደረጉ ግምገማዎች**

በህዝብ ወጪ ለሚደረግ የልጅዎን ገለልተኛ የሆነ ትምህርታዊ ግምገማ ካገኙ ወይም በግል ወጪ ያገኙትን የልጅዎን ግምገማ ከትምህርት ዲቪዥን ጋር ካካፈሉ፡-

1. ለልጅዎ ነጻ እና ተገቢ የሆነ የሕዝብ ትምህርት (FAPE) አቅርቦትን በተመለከተ በሚደረጉ ማናቸውም ውሳኔዎች ፣ የትምህርት ዲቪዥንዎ ገለልተኛ የሆነ ትምህርታዊ ግምገማ መመዘኛዎችን እስካሟላ ድረስ የልጅዎን የግምገማ ውጤት ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል። <u>**እና**</u>

2. እርስዎ ወይም የትምህርት ዲቪዥንዎ ልጅዎን በሚመለከት ግምገማውን በፍትህ ሂደት ችሎት እንደ ማስረጃ ማቅረብ ይችላሉ።

**በችሎት ሹሞች የተደረጉ የግምገማ ጥያቄዎች**

የችሎት ሹም እንደ የፍትህ ሂደት ችሎት አካል ስለልጅዎ ገለልተኛ የሆነ ትምህርታዊ ግምገማ ከጠየቀ፣ የግምገማው ዋጋ በህዝብ ወጪ መሆን አለበት።

**የትምህርት ዲቪዥን መስፈርቶች**

ገለልተኛ የሆነ ትምህርታዊ ግምገማ በህዝብ ወጪ ከሆነ፣ ግምገማው የተገኘበት መመዘኛ፣ የግምገማው ቦታ እና የፈታኙን ብቃትን ጨምሮ፣ በትምህርት ዲቪዥኑ ተነሳሽነት የሚደረግ ግምገማ ከሚጠቀምባቸው መመዘኛዎች ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት (እነዚያ መመዘኛዎች ከገለልተኛ የሆነ ትምህርታዊ ግምገማ መብትዎ ጋር የሚጣጣሙ መሆን አለባቸው።)

ከላይ ከተገለጹት መመዘኛዎች በስተቀር፣ የትምህርት ዲቪዥን በህዝብ ወጪ ገለልተኛ የሆነ ትምህርታዊ ግምገማ ከማግኘት ጋር የተያያዙ ሁኔታዎችን ወይም የጊዜ ገደቦችን ማስገደድ አይችልም።

## የመረጃ ምስጢራዊነት

የቨርጂኒያ "የተማሪ ስኮላስቲክ መዝገቦች አስተዳደር" ሰነድ https://www.doe.virginia.gov/?navid=257 ላይ ማግኘት ይችላሉ።

## ትርጓሜዎች

***የመረጃ ሚስጥራዊነት*** በሚለው ርዕስ ስር ጥቅም ላይ እንደዋለ፡-

- *ማጥፋት* ማለት አካላዊ ማጥፋት ወይም መረጃው የግል ማንነት እንደማያሳይ ለማድረግ የግል ማንነት የሚለዩ መረጃዎችን ማስወገድ ማለት ነው።

- *የትምህርት መዛግብት ማለት* በ34 CFR ክፍል 99 (የ1974፣20 U.S.C. 1232g የቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና ግላዊነት ድንጋጌ የአፈጻጸም ደንቦች (FERPA))በ "የትምህርት መዛግብት" ትርጉም ስር የተሸፈኑ የመዛግብት አይነት ማለት ነው።

## የግል ማንነት የሚገልጹ መረጃዎች

***የግል ማንነት የሚገልጹ መረጃዎች*** የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- የልጅዎ ስም፣ እንደወላጅ የእርስዎ ስም ወይም የሌላ የቤተሰብ አባል ስም፣
- የልጅዎ አድራሻ፣
- የግል መገለጫ እንደ የልጅዎ ሶሻል ሴኩሪቲ ቁጥር ወይም የተማሪ መታወቂያ ቁጥር፣ ***ወይም***
- ልጅዎን በተመጣጣኝ እርግጠኝነት ለመለየት የሚያስችሉ የግል ባህሪያት ወይም ሌሎች የመረጃዎች ዝርዝር።

## ማሳወቂያ ለወላጆች

**ስለልጅዎ መረጃ በስቴት እና በአካባቢው የትምህርት ዲቪዥን እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል እና በሚስጥር እንደሚጠበቅ በስቴቱ እንዲነገርዎት መብት አልዎት።**

የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE)፣ ስለ የግል ማንነት የሚገልጹ መረጃዎች ግላዊነት ለወላጆች ሙሉ ለሙሉ ለማሳወቅ የሚከተሉትን ያካተተ በቂ ማሳወቂያ መስጠት አለበት፤

1. ማሳወቂያው በቨርጂኒያ ውስጥ ባሉ የተለያዩ የህዝብ ቡድኖች የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች ምን ያህል እንደተጻፈ መግለጫ፣

2. የግል መለያ መረጃዎች የተያዙባቸው ልጆች ፣ የሚፈለጉትን የመረጃ ዓይነቶች፣ ቨርጂኒያ መረጃውን ለመሰብሰብ የምትጠቀምባቸው ዘዴዎች (መረጃ ከማን እንደተሰበሰቡ የሚያሳዩ ምንጮችን ጨምሮ) እና መረጃው ጥቅም ላይ የሚውሉት ምን ላይ እንደሆነ የሚያሳይ መግለጫ፣

3. ስለ ማከማቻ፣ ለሶስተኛ ወገኖች ይፋ ማድረግ፣ ማቆየት እና የግል መለያ መረጃን ማጥፋትን በተመለከተ ተሳታፊ ኤጀንሲዎች መከተል ያለባቸው ፖሊሲዎች እና ሂደቶች ማጠቃለያ፤ ***እና***

4. በቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና ግላዊነት ድንጋጌ (FERPA) እና በ 34 CFR ክፍል 99 ውስጥ ያሉትን የአፈጻፀም ደንቦቹን ጨምሮ ይህንን መረጃ በተመለከተ የወላጆች እና የልጆች መብቶች መግለጫ።

ከማንኛውም ዋና የመለየት፣ የማግኘት ወይም የግምገማ እንቅስቃሴ በፊት (እንዲሁም "ቻይልድ ፋይንድ" በመባልም ይታወቃል) ፣ የትምህርት ዲቪዥኖች ማሳወቂያውን በጋዜጦች ወይም በሌላ ሚዲያ ወይም በሁለቱም ላይ በማተም ወይም በቂ ስርጭት ባላቸው መንገዶች ስለ የልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚያስፈልጋቸው ልጆችን የማግኘት፣ የመለየት እና የመገምገም እንቅስቃሴዎች ወላጆችን ማሳወቅ አለባቸው።

**የተደራሽነት መብቶች**

**የልጅዎን መዛግብት የመርመር መብት አልዎት።**

በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ስር፣ የተሰበሰቡ፣ የተቀመጡ ወይም በትምህርት ዲቪዥንዎ ጥቅም ላይ የሚውሉትን ከልጅዎ ጋር የተያያዙ የትምህርት መዝገቦችን እንዲፈትሹ እና እንዲገመግሙ የትምህርት ዲቪዥንዎ[2] መፍቀድ አለበት። የትምህርት ዲቪዥኑ በልጅዎ ላይ ያሉ ማናቸውንም የትምህርት መዛግብትን ለመፈተሽ እና ለመገምገም ያቀረቡትን ጥያቄ ያለአላስፈላጊ መዘግየት ማስተናገድ አለበት፤ እና የተናጠል ትምህርት ፕሮግራምን (IEP) ወይም ማንኛውንም ኢሻራዊ የፍትህ ሂደትን በሚመለከት ከማንኛውም ስብሰባ በፊት (የመፍትሄ ስብሰባ ወይም የስነ ምግባር ችሎትን ጨምሮ) በማንኛውም ሁኔታ ከጠየቁበት ከ45 የመቁጠሪያ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ማስተናገድ አለበት።

የትምህርት መዛግብትን የመመርመር እና የመገምገም መብትዎ የሚከተሉትን ያካትታል፦

1. የማብራሪያ እና የመዛግብትን ትርጓሜ ለማግኘት ላቀረቡት ምክንያታዊ ጥያቄዎች፣ ከትምህርት ዲቪዥን ምላሽ የማግኘት፤
2. እነዚያ ቅጂዎች ቀድመው ካልተቀበሉ በስተቀር መዛግብቱን በብቃት መመርመር እና መገምገም ካልቻሉ የትምህርት ዲቪዥኑ የመዛግብቱን ቅጂ እንዲሰጥዎት የመጠየቅ፤ <u>እና</u>
3. የእርስዎ ተወካይ መዛግብቱን እንዲመረምር እና እንዲገመግም የማድረግ መብት አልዎት።

እንደ ህጋዊ አሳዳጊነት፣ መለያየት እና ፍቺ ያሉ ጉዳዮችን በሚመለከተው የቨርጂኒያ ህግ መሰረት ስልጣን የለዎትም ካልተባለ በስተቀር፣ የትምህርት ዲቪዥኑ ከልጅዎ ጋር የተያያዙ መዛግብትን የመመርመር እና የመገምገም ስልጣን እንዳለዎት ታሳቢ ያደርጋል።

**የመዳረሻ መዝገብ**

**የልጅዎ የትምህርት መዛግብት ከእርስዎ ወይም በትምህርት ዲቪዥኑ ሰራተኛ ውጪ በሌላ ሰው ከታየ፣ የልጅዎን መዝገብ የሚይዘው ትምህርት ቤት፣ የልጅዎን መዝገብ እነማን እንዳዩት እና መቼ እና ለምን እንደገመገሙት መዝግቦ መያዝ አለበት።**

እያንዳንዱ የትምህርት ዲቪዥን፣ በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ስር የተሰበሰቡ፣ የተቀመጡ ወይም ጥቅም ላይ የዋሉ የትምህርት መዛግብትን  የተጠቀሙበት ወገኖችን (ከወላጆች እና ከተፈቀደላቸው የትምህርት ቤቱ ክፍል ሰራተኞች በስተቀር) ስም ጨምሮ፣ መዝገቡ የታየበት ቀን ፣ እና ወገኑ መዛግብቱን እንዲጠቀም የተፈቀደለት ዓላማን ጨምሮ መዝግቦ ማስቀመጥ አለበት።

[2] መዛግብትን በተመለከተ አሰራሮች "ተሳታፊ ኤጀንሲዎች" ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ። በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ክፍል B ስር "ተሳታፊ ኤጀንሲ" ማለት ማንኛውም የትምህርት ዲቪዥን፣ ኤጀንሲ ወይም ተቋም በግል የሚለይ መረጃን የሚሰበስብ፣ የሚያስቀምጥ ወይም የሚጠቀም ወይም መረጃ የሚሰጥ ማለት ነው። ነገር ግን፣ ይህ ሰነድ የሚያተኩረው ወላጆች ከአካባቢው የትምህርት ዲቪዥን ጋር ያላቸውን ተሳትፎ በመሆኑ፣ "ተሳታፊ ኤጀንሲ" ሳይሆን፣ "የአከባቢ ትምህርት ዲቪዥን" የሚለው ቃል ጥቅም ላይ ውሏል።

## ከአንድ በላይ ልጆች መዛግብት

የትኛውም የትምህርት መዝገብ ከአንድ በላይ ልጆች ላይ መረጃን ያካተተ ከሆነ፣ የነዚያ ልጆች ወላጆች ከልጃቸው ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ብቻ የመመርመር እና የመገምገም ወይም ስለዚያ የተለየ መረጃ የማወቅ መብት አላቸው።

## የመረጃ ዓይነቶች እና መገኛ ቦታዎች ዝርዝር

በተጠየቀ ጊዜ፣ እያንዳንዱ የትምህርት ዲቪዥን በኤጀንሲው የተሰበሰቡ፣ የተቀመጡ ወይም የሚገለገሉባቸውን የትምህርት መዛግብት ዓይነቶች እና ቦታዎች ዝርዝር ሊሰጥዎ ይገባል።

## ክፍያዎች

ክፍያው መዛግብቱን በብቃት የመመርመር እና የመገምገም መብትዎን የማይጋፋ ከሆነ፣ በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ስር እያንዳንዱ የትምህርት ዲቪዥን ለእርስዎ ያዘጋጁት የመዛግብት ቅጂዎች ክፍያ ሊያስከፍል ይችላል።

የትምህርት ዲቪዥን በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ስር መረጃን ለመፈለግ ወይም ለማውጣት ክፍያ ሊያስከፍል አይችልም።

## በወላጆች ጥያቄ መሰረት መዛግብትን ማሻሻል

**መዝገቡ ትክክል አይደለም ብለው ካሰቡ ወይም የልጅዎን ግላዊነት የሚጥስ ከሆነ፣ የልጅዎ የትምህርት መዝገብ እንዲቀየር የመጠየቅ መብት አለዎት።**

በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ስር የተሰበሰበው፣ የተቀመጠው ወይም ጥቅም ላይ የዋለው የልጅዎ የትምህርት መዛግብት ውስጥ ያለው መረጃ ትክክል ያልሆነ፣ አሳሳች ወይም የልጅዎን ግላዊነት ወይም ሌሎች መብቶች የሚጥስ ነው ብለው ካመኑ፣ መረጃውን የሚይዘው የትምህርት ዲቪዥን መረጃውን እንዲለውጥ መጠየቅ ይችላሉ።

የትምህርት ዲቪዥኑ ጥያቄዎን በደረሰው ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ በጥያቄዎ መሰረት መረጃውን ለመቀየር ወይም ላለመቀየር መወሰን አለበት።

የትምህርት ዲቪዥኑ በጥያቄዎ መሰረት መረጃውን ለመለወጥ ፈቃደኛ ካልሆነ፣ እምቢታውን ማሳወቅ እና ለዚህ ዓላማ **ችሎት የማግኘት እድል** በሚል ርዕስ በተገለጸው መሰረት የችሎት መብት እንዳለዎት ምክር መስጠት አለበት።

## ችሎት የማግኘት እድል

**የልጅዎ የትምህርት መዝገብ እንዲቀየር ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ ከተደረገ፣ ችሎት የማግኘት መብት አልዎት።**

የትምህርት ዲቪዥኑ፣ በጥያቄዎ መሰረት፣ ልጅዎን በሚመለከት በትምህርት መዛግብት ውስጥ ያለውን መረጃ ትክክል ያልሆነ፣ አሳሳች፣ ወይም በሌላ መልኩ የልጅዎን ግላዊነት ወይም ሌሎች መብቶች የሚጥስ አለመሆኑን ለማረጋገጥ ችሎት የማግኘት እድል ሊሰጥዎ ይገባል።

## የችሎት አሰራሮች

በትምህርት መዛግብት ውስጥ ያለውን መረጃ ለመቃወም ችሎት መከናወን ያለበት በቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና የግላዊነት ድንጋጌ (FERPA) ስር ባሉ የችሎቶች አሰራሮች መሰረት ነው።

በቨርጂኒያ፣ የትምህርት ዲቪዥን በዚህ ሰነድ "የፍትህ ሂደቶች" በሚል ክፍል ውስጥ በተገለፀው መሰረት የፍትህ ሂደት ችሎት ሂደቶችን አማራጭ የመጠቀም ወይም ከቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና የግላዊነት ድንጋጌ (FERPA) ጋር እስከተስማሙ ድረስ የራሳቸውን የአሰራር ሂደቶች መጠቀም ይችላሉ።

## የችሎት ውጤት

**በችሎት ምክንያት የልጅዎ የትምህርት መዝገብ እንዲቀየር ወይም በመዝገቡ ውስጥ ካለው መረጃ ጋር እንደማይስማሙ የሚገልጽ መግለጫ በልጅዎ በትምህርት መዝገብ ውስጥ የማካተት መብት አልዎት።**

ከችሎቱ በኋላ መረጃው የተሳሳተ ፣ አሳሳች ወይም በሌላ መንገድ የልጅዎን ግላዊነት ወይም ሌሎች መብቶች የሚጥስ ሆኖ ከተገኘ፣ የትምህርት ዲቪዥኑ መረጃውን በዛ መሰረት መለወጥ እና በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት።

ከችሎቱ በኋላ መረጃው ትክክል ያልሆነ፣ አሳሳች ወይም በሌላ መልኩ የልጅዎን ግላዊነት ወይም ሌሎች መብቶች የሚጥስ ሆኖ ከልተገኘ፣ የትምህርት ዲቪዥኑ በዚህ ጉዳይ ላይ ስለ መረጃው አስተያይትዎን የሚገልጽ መግለጫ ወይም በውሳኔው የማይስማሙትን ማንኛውንም ምክንያት የማቅረብ መብት እንዳለዎት ማሳወቅ አለበት። ይህ መግለጫ የትምህርት ዲቪዥኑ በልጅዎ ላይ በሚያስቀምጠው መዛግብት ውስጥ መቀመጥ አለበት።

በልጅዎ መዝገብ ውስጥ የሚቀመጠው እንዲህ ዓይነቱ ማብራሪያ፦

1. የትምህርት ዲቪዥኑ የልጅዎ መዛግብት እስካስቀመጠበት ድረስ፣ መዝገቡ ወይም ክርክር የተደረገበት ክፍል በትምህርት ዲቪዥኑ እንደ የልጅዎ አንድ የመዛግብት አካል ሆኖ እንዲቀመጥ፣ <u>እና</u>

2. የትምህርት ዲቪዥኑ የልጅዎን መዛግብት ወይም ክርክር የተደረገበት ክፍል ለማንኛውም አካል ካሳወቀ፣ ለዚያ አካልም ማብራሪያው መገለጽ አለበት።

## የግል ማንነት የሚገልጹ መረጃዎችን ይፋ የማድረግ ፈቃድ

**ልጅዎን የሚለይ መረጃ ለመልቀቅ ፈቃድ የመስጠት መብት አልዎት። በአንዳንድ ሁኔታዎች የእርስዎ ፈቃድ አያስፈልግም።**

መረጃው በትምህርት መዛግብት ውስጥ እስካልተያዘ ድረስ እና ያለወላጅ ፈቃድ ይፋ ማድረጉ በቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና ግላዊነት ድንጋጌ (FERPA) ስር ካልተፈቀደ በቀር፣ የግል ማንነት የሚገልጹ መረጃዎች ከተሳታፊ ኤጀንሲዎች ኃላፊዎች ውጪ ለሌላ አካላት ከመገለጹ በፊት የእርስዎ ፈቃድ መገኘት አለበት። ከዚህ በታች ከተገለጹት ሁኔታዎች በስተቀር፣ የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌን (IDEA) መስፈርት ለማሟላት የግል ማንነት የሚገልጹ መረጃዎች ለተሳታፊ ኤጀንሲዎች ባለስልጣናት ከመለቀቁ በፊት የእርስዎ ፈቃድ አያስፈልግም።

በቨርጂኒያ ህግ መሰረት የግል ማንነት የሚገልጹ መረጃዎች ለተሳታፊ ኤጀንሲዎች ባለስልጣናት ወይም ለሽግግር አገልግሎት ለሚሰጡ ለመከፈል ከመለቀቁ በፊት ለአካለ መጠን ከደረሰ ልጅ ወይም የእርስዎ ፈቃድ ማግኘት አለበት።

ልጅዎን እርስዎ ከሚኖሩበት የትምህርት ዲቪዥን ውጪ በሌላ የግል ትምህርት ቤት በራስዎት ፈቃድ ብቻ ካስመዘገቡት ፣ ስለልጅዎ የግል ማንነት የሚገልጹ መረጃዎች የግል ትምህርት ቤቱ ባለበት የትምህርት ዲቪዥኑ እና እርስዎ በሚኖሩበት የትምህርት ዲቪዝን ውስጥ ባሉ ባለሥልጣናት መካከል ከመለቀቁ በፊት የእርስዎ ፈቃድ መገኘት አለበት።

## ከለላዎች

**የትምህርት ዲቪዥንዎ የልጅዎን የትምህርት መዛግብት በሚስጥር እንደሚያስቀምጥ የመጠበቅ መብት አልዎት።**

እያንዳንዱ የትምህርት ዲቪዥን የግል ማንነት የሚገልጹ መረጃዎችን በሚሰበሰብበት፣ በሚያከማችበት፣ በሚያካፍልበት እና በሚያጠፋበት ጊዜ ሚስጥራዊ በሆነ መንገድ መሆን አለበት።

በእያንዳንዱ የትምህርት ዲቪዥን፣ አንድ ባለስልጣን የማንኛውንም የግል ማንነት የሚገልጹ መረጃዎችን ሚስጥራዊነት የመጠበቅ ሃላፊነት መውሰድ አለበት።

ሁሉም የግል ማንነት የሚገልጹ መረጃዎችን የሚሰበስቡ ወይም የሚጠቀሙ ሰዎች፣ በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) እና በቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና የግላዊነት ድንጋጌ (FERPA) ስር ሚስጥራዊነትን በተመለከተ የቨርጂኒያ ፖሊሲዎችን እና ሂደቶችን ስልጠና ወይም መመሪያ ማግኘት አለባቸው።

እያንዳንዱ የትምህርትዲቪዥን፣ ለህዝብ ቁጥጥር የሚውል፣ በኤጀንሲው ውስጥ ያሉ የግል ማንነት የሚገልጹ መረጃዎችን ማየት የሚችሉ ሠራተኞች ስም እና የሥራ ቦታ ወቅታዊ ዝርዝር መያዝ አለበት።

## መረጃን ማጥፋት

**የልጅዎ የትምህርት መረጃ አስፈላጊነቱ በሚያበቃበት ጊዜ፣ የትምህርት ዲቪዥኑን መረጃውን እንዲያጠፋ የመጠየቅ መብት አልዎት።**

ለልጅዎ ትምህርታዊ አገልግሎቶችን ለመስጠት የተሰበሰበው ፣ የተቀመጠው ወይም ጥቅም ላይ የዋለው የግል ማንነት የሚገልጹ መረጃዎችን አስፈላጊነቱ በሚያበቃበት ጊዜ፣ የትምህርት ዲቪዥንዎ ማሳወቅ አለበት።

በጥያቄዎ መሰረት መረጃው መጥፋት አለበት። ነገር ግን፣ የልጅዎ ስም፣ አድራሻና የስልክ ቁጥር፣ የትምህርት ውጤቶች፣ የመገኘት መዝገብ፣ የተማሩበት ክፍል፣ የክፍል ደረጃ እና ትምህርት ያጠናቀቁበት አመት ቋሚ መዝገብ ላይ ያለ ጊዜ ገደብ ሊቆይ ይችላል።

# የግጭት አፈታት አማራጮች

ስለ አሠራሮች ተጨማሪ መረጃ እና ለሽምግልና፣ የቅሬታ አፈታት እና የፍትህ ሂደት ሥርዓቶች የሚያስፈልጉ ቅጾችን ለማግኘት ድህረ ገጹን https://www.doe.virginia.gov/? navid=652, or by contacting VDOE. ይጎብኙ ወይም የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያን (VDOE) ያግኙ።

## <u>ሽምግልና</u>

***ወደ የፍትህ ሂደት ችሎት ጥያቄ የሚያመሩ ጉዳዮችን ጨምሮ አለመግባባቶችን ለመፍታት ሽምግልና የመጠየቅ መብት አልዎት። እርስዎም ሆኑ የትምህርት ዲቪዥንዎ ሽምግልናን ያለመቀበል መብት አላችሁ። የሽምግልና ጥያቄዎ የፍትህ ሂደት ጥያቄዎን ሊያዘገየው ወይም ሊያቆመው አይችልም።***

### አጠቃላይ

የፍትህ ሂደት ጥያቄ ከመቅረቡ በፊት የሚነሱ ጉዳዮችን ጨምሮ፣ እርስዎ እና የትምህርት ዲቪዥኑ በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ስር ያለ ማንኛውንም ጉዳይ በሚመለከት አለመግባባቶችን ለመፍታት እንዲችሉ የትምህርት ዲቪዥኑ የሽምግልና እድል እንዲኖር ማድረግ አለበት። ስለዚህ፣ ***ለፍትህ ሂደት የችሎት ጥያቄ ማቅረብ*** በሚለው ርዕስ ላይ እንደተገለጸው፣ የፍትህ ሂደት ጥያቄ ቢያቀርቡም ባያቀርቡም በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ስር ያሉ አለመግባባቶችን ለመፍታት የሽምግልና እድል ይኖራል።

### መስፈርቶች

የሽምግልና ሂደት:-

1. በእርስዎ እና በትምህርት ዲቪዥኑ ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፤
2. የፍትህ ሂደት ችሎት የማግኘት መብትዎን ወይም በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ስር ያልዎትን ማንኛውንም መብቶች ለመከልከል ወይም ለማጓተት ጥቅም ላይ አይውልም፤ **<u>እና</u>**
3. በውጤታማ የሽምግልና ቴክኒኮች በሰለጠነ ብቁ እና ገለልተኛ አስታራቂ ይካሄዳል።

ወላጆች የሽምግልና ጥቅሞችን እንዲረዱ የትምህርት ዲቪዥኑ ወላጆች እና የሽምግልና ሂደቱን ላለመጠቀም ለሚመርጡ ትምህርት ቤቶች፣ ገለልተኛ ከሆነ ወገን ጋር ለወላጆች በሚመች ጊዜ እና ቦታ የመገናኘት እድልን የሚሰጥ ሂደቶችን ሊያዘጋጅ ይችላል፤ ገለልተኛ የሆነ ወገኑ:-

1. አግባብ ካለው አማራጭ የግጭት አፈታት አካል፣ ወይም የወላጅ ማሰልጠኛ እና የመረጃ ማዕከል ወይም በቨርጂኒያ ውስጥ ካለው የማህበረሰብ የወላጅ መገልገያ ማእከል ጋር ውል ውስጥ ያለ፤ **<u>እና</u>**
2. የሽምግልና ሂደት ጥቅሞች ለእርስዎ የሚያብራራ እና እንዲጠቀሙበት የሚያበረታታዎት ነው።

የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) ብቁ ሽምጋዮች የሆኑ እና የልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን አቅርቦትን የሚመለከቱ ህጎችን እና ደንቦችን የሚያውቁ የሰዎች ዝርዝር ሊኖረው ይገባል። የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) ሽምጋዮችን በጊዜ በማቀያየር መምረጥ አለበት።

የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) የሽምግልና ክፍለ ጊዜ ወጪዎችን ጨምሮ ለሽምግልና ሂደት የወጡ ወጪዎችን የመሸፈን ኃላፊነት አለው።

በሽምግልና ሂደት ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ስብሰባ በጊዜ መርኃግብር ተይዞለት ለርስዎ እና ለትምህርት ዲቪዥኑ በሚመች ቦታ መካሄድ አለበት።

እርስዎ እና የትምህርት ዲቪዥኑ አለመግባባቶችን በሽምግልና ሂደት ከተፈቱ በኋላ፣ ሁለቱም ወገኖች መፍትሄውን የሚያስቀምጥ ህጋዊ አስገዳጅ እናም የሚከተሉትን የሚያካትት ስምምነት ማድረግ አለባቸው :-

1. በሽምግልና ሂደት ውስጥ የተከሰቱት ሁሉም ውይይቶች ሚስጥራዊ ሆነው እንደሚቆዩ እና በማናቸውም ቀጣይ የፍትህ ሂደት ችሎት ወይም የፍትሐ ብሄር ክሶች ላይ እንደማስረጃነት መጠቀም እንደማይቻል የሚገልጽ፤ **እና**

2. በእርስዎ እና በትምህርት ዲቪዥኑ የማስገደድ ስልጣን ባለው የትምህርት ዲቪዥኑ ተወካይ የተፈረመ።

በጽሁፍ የቀረበ እና የተፈረመ የሽምግልና ስምምነት በማንኛውም የቨርጂኒያ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት (ይህንን አይነት ጉዳይ ለመስማት ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት) ወይም በፌደራል ወፍርድ ቤት ተፈጻሚ ይሆናል።

### የሽምጋይ ገለልተኝነት

ሽምጋዩ:-

1. በልጅዎ ትምህርት ወይም እንክብካቤ ላይ በሚሳተፈው የትምህርት ዲቪዥን ወይም ለልጅዎ ቀጥተኛ አገልግሎት እየሰጠ ባለው የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) ሰራተኛ ሊሆን አይችልም፤ **እና**
2. ከሽምጋዩ ተጨባጭነት ባህሪ ጋር የሚጋጭ የግል ወይም ሙያዊ ፍላጎት ሊኖረው አይገባም።

አንድ ለሽምግልና ብቁ የሆነ ሰው በዋናነት እንደ ሽምጋይ ለማገልገል በትምህርት ዲቪዥኑ ወይም በስቴት ኤጀንሲው የሚከፈል በመሆኑ የኤጀንሲው ወይም የትምህርት ዲቪዥኑ ተቀጣሪ አይደለም።

## <u>የስቴት የቅሬታ አፈታት አሰራሮች</u>

### የፍትህ ሂደት ችሎት እና የስቴት ቅሬታ አፈታት አሰራሮች መካከል ያለው ልዩነት

---

**ከሽምግልና በተጨማሪ፣ ከትምህርት ዲቪዥኑ ጋር የተፈጠሩት አለመግባባቶችን ለመፍታት የስቴቱን ቅሬታ አፈታት ሂደት ወይም የፍትህ ሂደት ችሎትን የመጠቀም መብት አልዎት። እነዚህ ዘዴዎች የተለያዩ አሰራሮች አሏቸው። ለምሳሌ፣ ወላጅ ወይም የትምህርት ዲቪዥን ብቻ የፍትህ ሂደት ችሎት መጠየቅ ይችላሉ። በሌላ በኩል፣ የስቴት ቅሬታ በማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት ሊቀርብ ይችላል።**

የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA)፣ ለስቴት ቅሬታዎች እና የፍትህ ሂደት ችሎት ጥያቄዎች የተለዩ ሂደቶችን ያስቀምጣል። ከዚህ በታች እንደተብራራው፣ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት በትምህርት ዲቪዥን፣ በቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) ወይም በማንኛውም የህዝብ ኤጀንሲ ላይ ማንኛውንም የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) መስፈርት ጥሷል በማለት የስቴት ቅሬታ ማቅረብ ይችላል። አካል ጉዳተኛ ልጅን ለመለየት፣ ግምገማ ወይም ትምህርታዊ ምደባ ሃሳብ ማቅረብ፣ አለመቀበል ወይም መቀየር ወይም ለልጁ ነጻ እና ተገቢ የሆነ የህዝብ ትምህርት (FAPE) አቅርቦትን በሚመለከት በማንኛውም ጉዳይ ላይ እርስዎ ወይም የትምህርት ዲቪዥን ብቻ የፍትህ ሂደት ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ።

የጊዜ ሰሌዳው በአግባቡ ካልተራዘመ በስተቀር በአጠቃላይ የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) ሰራተኞች የስቴት ቅሬታን በ60-የቀን መቁጠሪያ ጊዜ ውስጥ መፍታት አለባቸው። የማያዳላ የፍትህ ሂደት ችሎት ሹም የፍትህ ሂደት ጥያቄን ሰምቶ (በመፍትሄ ስብሰባ ወይም በሽምግልና ካልተፈታ) እና በዚህ ሰነድ ***የመፍትሄ ሂደት*** በሚል ርዕስ ስር እንደተገለጸው፣ የመፍትሄው ጊዜ ካለቀ በኋላ በ45-የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ የጽሁፍ ውሳኔ መስጠት አለበት። የችሎቱ ሹም በእርስዎ ወይም በትምህርት ዲቪዥኑ ጥያቄ መሰረት የተወሰነ የጊዜ ሰሌዳ ማራዘሚያ ሊሰጥ ይችላል።

## የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) የቅሬታ አፈታት አሰራር ተግባራዊ

**አጠቃላይ**

የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) ለሚከተሉት በጽሁፍ የተቀመጠ የአፈታት አሠራር ሊኖረው ይገባል፦

- ከሌላ ስቴት የመጣ ድርጅት ወይም ግለሰብ ያቀረበውን ቅሬታ ጨምሮ ማንኛውንም መፍትሔ የሚሰጥበት አሠራር፤
- ለቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) የቅሬታ ማመልከቻ አሠራር፤
- የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) ቅሬታ አፈታት አሰራሮች ለወላጆች እና ለሌሎች ፍላጎት ላላቸው ግለሰቦች፣ የወላጅ ማሰልጠኛ እና የመረጃ ማዕከላትን፣ የጥበቃ እና ተሟጋች ኤጀንሲዎችን፣ ገለልተኛ የመኖሪያ ማዕከላትን እና ሌሎች ተገቢ አካላትን ጨምሮ በሰፊው ማሰራጨት።

የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) የቅሬታ አፈታት አሰራሮች https://www.doe.virginia.gov/?navid=248 ላይ ማግኘት ይችላሉ።

**ተገቢ አገልግሎቶችን ላለመስጠቱ የሚደረጉ እርምጃዎች**

የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) ተገቢውን አገልግሎት አለመስጠቱን ያወቀበትን የስቴት ቅሬታ ለመፍታት፣ የሚከተሉትን ላይ መነጋገር አለበት፦

1. የልጁን ፍላጎቶች ለማሟላት ተገቢውን የእርምት እርምጃን ጨምሮ ተገቢውን አገልግሎት አለመስጠቱን፣ <u>እና</u>
2. ለወደፊቱ ተገቢውን አገልግሎት ለሁሉም አካል ጉዳተኛ ልጆች ማቅረብ።

## አነስተኛው የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) የቅሬታ አፈታት አሰራሮች

**የጊዜ ገደብ፤ አነስተኛ አሰራሮች**

የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) የሚከተሉትን ለማካናወን፣ በቅሬታ አፈታት አሰራሮች ውስጥ ቅሬታ ከቀረበ በኋላ የ60 የቀን መቁጠሪያ ቀናት የጊዜ ገደብ ማካተት አለበት፦

1. የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) ምርመራ አስፈላጊ መሆኑን ከወሰነ በኋላ፣ በጣቢያው ላይ ገለልተኛ ምርመራ ለማካሄድ፤
2. ቅሬታ አቅራቢው በቅሬታው ላይ ስላሉት ክሶች በቃልም ሆነ በጽሁፍ ተጨማሪ መረጃ እንዲያቀርብ እድል ለመስጠት፤

3. የትምህርት ዲቪዥኑ ለተደረገው ቅሬታ ቢያንስ የሚከተሉትን ጨምሮ ምላሽ እንዲሰጥ እድል ለመስጠት፡- (ሀ) በትምህርት ዲቪዥኑ ምርጫ፣ ቅሬታውን ለመፍታት ሃሳብ ለማቅረብ፤ **<u>እና</u>** (ለ) ቅሬታ ላቀረበው ወላጅ እና ኤጀንሲው በፈቃደኝነት ወደ ሽምግልና ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ እድል ለመስጠት፤

4. ሁሉንም አስፈላጊ መረጃዎችን ለመከለስ እና የትምህርት ዲቪዥኑ የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌን (IDEA) መስፈርት እየጣሰ እንደሆነ ገለልተኛ የሆነ ውሳኔ ለማድረግ፤ **<u>እና</u>**

5. ለቅሬታ አቅራቢው እያንዳንዱን ቅሬታ የሚመለከት እና የሚከተሉትን ውሳኔ የያዘ በጽሁፍ ለማቅረብ፡- (ሀ) የእውነታ ግኝቶች እና መደምደሚያዎች፣ **<u>እና</u>** (ለ) የVDOE የመጨረሻ ውሳኔ ምክንያቶች

**የጊዜ ማራዘሚያ፤ የመጨረሻ ውሳኔ እና ውሳኔውን ማስፈጸም**

ከላይ የተገለጹት የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) አሰራሮች የሚከተሉትንም

1. በ60 የቀን መቁጠሪያ-ቀን የጊዜ ገደብ እንዲራዘም የሚፈቀደው፡- (ሀ) ከልዩ ግዛት ቅሬታ ጋር በተያያዘ ልዩ ሁኔታዎች ካሉ **<u>ወይም</u>** (ለ) ወላጅ እና የትምህርት ዲቪዥኑ ጉዳዩን በሽምግልና ወይም በአማራጭ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ለመፍታት ጊዜውን ለማራዘም በፈቃደኝነት ከተስማሙ ብቻ ነው።

2. የVDOE የመጨረሻ ውሳኔን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማስፈጸም የሚያስችሉ አሰራሮችን፣ አስፈላጊ ከሆነ የሚከተሉትን ጨምሮ፣ ማካተት፡- (ሀ) የቴክኒካል ድጋፍ ተግባራት (ለ) ድርድሮች **<u>እና</u>** (ሐ) የውሳኔውን መከበር ለማረጋገጥ የማስተካከያ እርምጃዎች።

**የስቴት ቅሬታዎች እና የፍትህ ሂደት ችሎቶች**

***የፍትህ ሂደት ጥያቄ ማመልከቻ ማስገባት*** በሚለው ርዕስ ስር እንደተገለጸው፣ የፍትህ ሂደት ችሎት ርዕሰ ጉዳይ የሆነ የስቴት ቅሬታ በጽሁፍ ከደረሰ ወይም የስቴቱ ቅሬታ አንድ ወይም ብዙ የዚህ ችሎት አካል የሆኑባቸው በርካታ ጉዳዮችን ከያዘ፣ የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) ችሎቱ እስኪያልቅ ድረስ የስቴቱን ቅሬታ ወይም በፍትህ ሂደት ችሎት ውስጥ የሚመለከተውን ማንኛውንም የስቴት ቅሬታ ወደ ጎን መተው አለበት። በስቴቱ ውስጥ ያለ ማንኛውም የፍትህ ሂደት ችሎት አካል ያልሆነ ቅሬታ ከላይ የተገለጹትን የጊዜ ገደቡን እና አሰራሮችን በመጠቀም መፈታት አለበት።

በስቴት ቅሬታ ላይ የተነሳው ጉዳይ ቀደም ሲል በፍትህ ሂደት ችሎት ከተመሳሳይ ወገኖች (እርስዎ እና የትምህርት ዲቪዥኑን) ጋር የተያያዘ ከሆነ፣ የፍትህ ሂደት ችሎቱ ውሳኔ በዚህ ጉዳይ ላይ አስገዳጅ ነው እና የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) ውሳኔው አስገዳጅ መሆኑን ለቅሬታ አቅራቢው ማሳወቅ አለበት።

የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) የትምህርት ዲቪዥን የፍትህ ሂደት ችሎትን ተግባራዊ አላደረገም የሚሉ ቅሬታዎችን መፍታት አለበት።

**ቅሬታ ማቅረብ**

---

| |
|---|
| **ለቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) ቅሬታ የማቅረብ መብት አልዎት ነገር ግን ቅሬታዎት የተወሰኑ መረጃ ማካተት አለበት።** |

አንድ ድርጅት ወይም ግለሰብ ከላይ በተገለጹት አሰራሮች መሰረት የተፈረመ የስቴት ቅሬታ ማቅረብ ይችላል። የስቴቱ ቅሬታ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

1. የትምህርት ዲቪዥን የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) መስፈርት ወይም ደንቦቹን እንደጣሰ የሚገልጽ ጽሁፍ፤
2. መግለጫው የተመሰረተባቸው እውነታዎች፤
3. የቅሬታ አቅራቢው ፊርማ እና አድራሻ መረጃ፤ እና
4. ቅሬታው በአንድ የተወሰነ ልጅ ላይ የተፈጸሙ ጥሰቶች ላይ ከሆነ፡-
   (ሀ) የልጁ ስም እና የልጁ መኖሪያ አድራሻ፤
   (ለ) ልጁ የሚማርበት የትምህርት ቤት ስም፤
   (ሐ) ቤት አልባ ልጅ ወይም ወጣት ከሆነ፣ ልጁ የሚገኝበት የመገናኛ መረጃ፣ እና ልጁ የሚማርበት የትምህርት ቤት ስም፤
   (መ) የችግሩን እውነታዎች ጨምሮ ልጁ ላይ የደረሰው የችግሩ ባህሪ መግለጫ፣ <u>እና</u>
   (ሠ) ቅሬታው በሚቀርብበት ጊዜ ቅሬታውን ላቀረበው አካል እስካወቀው ድረስ እና በተገኘው መጠን የቀረበው ለችግሩ መፍትሄ።

***የስቴት የቅሬታ አፈታት አሰራር ተግባራዊ ስለማድረግ*** በሚለው ርዕስ ስር በተገለጸው መሰረት፣ ቅሬታው ከገባበት ቀን ከአንድ አመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የተፈፀመ ጥሰት መከሰቱን የሚገልጽ መሆን አለበት ።

የስቴቱን ቅሬታ የሚያቀርብ አካል የቅሬታውን ለቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) በሚያቀርብበት ጊዜ ወደ ልጁን የሚያገለግለው የትምህርት ዲቪዥኑ ግልባጭ መላክ አለበት።

በቨርጂኒያ፣ የቅሬታው አካላት (እርስዎ እና የትምህት ዲቪዥኑ) ውሳኔው በወጣ በ30 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ የመጨረሻውን የቅሬታ ውሳኔ ይግባኝ የመጠየቅ መብት አላችሁ። የቅሬታ ይግባኝ ገምጋሚው ውሳኔ የመጨረሻ ነው። ይህንን የይግባኝ ሂደት በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ከላይ በተጠቀሰው የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) ድህረ-ገጽ ይጎብኙ ወይም የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያን (VDOE) ያግኙ።

## <u>የፍትህ ሂደት</u> <u>አሰራሮች</u>

### ለፍትህ ሂደት የችሎት ጥያቄ ማቅረብ

**እርስዎ እና ትምህርት ቤቱ ስለ ልጅዎ ትምህርት መስማማት ካልቻላችሁ የፍትህ ሂደት ችሎት የመጠየቅ መብት አልዎት። ስለ ነጻ ወይም ዝቅተኛ ወጪ የህግ እርዳታ መረጃ የማግኘት መብት አልዎት።**

**አጠቃላይ**

እርስዎ ወይም የትምህርት ዲቪዥኑ የልጅዎን የመለያ፣ ግምገማ ወይም ትምህርታዊ ምደባ ሃሳብ ማቅረብ ወይም አለመቀበል ወይም መለወጥ ወይም ለልጅዎ ነጻ እና ተገቢ የህዝብ ትምህርት (FAPE) አቅርቦትን በሚመለከት በማንኛውም ጉዳይ ላይ የፍትህ ሂደት ጥያቄ ማቅረብ ትችላላችሁ።

የፍትህ ሂደት ጥያቄው፣ እርስዎ ወይም የትምህርት ዲቪዥኑ የፍትህ ሂደት ጥያቄ መሰረት የሆነውን የተጠረጠረውን ተግባር እርስዎ ወይም የትምህርት ዲቪዥኑ ካወቁበት ወይም ማወቅ ከነበረባቸው ከሁለት አመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የተፈፀመ ጥሰት መሆን አለበት።

ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ መሰረት የፍትህ ሂደት ጥያቄ ማቅረብ ያልቻሉበት ምክንያት ከሚከተሉት ውስጥ ከሆነ፣ የጊዜ ገደቡ እርስዎን አይመለከትም፤

1. የትምህርት ዲቪዥኑ በተለይ በጥያቄው ውስጥ የተገለጹትን ጉዳዮች እንደፈቱ አድርጎ በተሳሳተ መንገድ ካቀረበ **ወይም**
2. የትምህርት ዲቪዥኑ በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ስር ለእርስዎ መግለጽ የነበረበትን መረጃ ከእርስዎ ከደበቀ።

### ለወላጆች መረጃ

እርስዎ ወይም የትምህርት ዲቪዥኑ የፍትህ ሂደት ጥያቄ ካቀረቡ **ወይም** መረጃውን ከጠየቁ፣ የትምህርት ዲቪዥኑ ማንኛውንም ነጻ ወይም በዝቅተኛ ወጪ የህግ እና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶችን መረጃ መስጠት አለበት። የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) በድህረ-ገጹ https://www.doe.virginia.gov/?navid=652 ላይ የሚገኙ እንደዚህ ያሉ የስቴት አቀፍ አገልግሎቶችን ዝርዝር መረጃ አለው።

በመቀጠል፣ "የፍትህ ሂደት ሰነዶች" በሚለው ርእስ ስር "የህግ/ለልዩ ትምህርት የአድቮኬሲ ቡድኖች እና ግብዓቶች " የሚለውን ይጫኑ።

የቨርጂኒያ ህግ፣ የፍትህ ሂደት ችሎት ላይ ተሳታፊ ወገኖች ጠበቃ ባልሆኑ ሰዎች እንዲወከሉ ይፈቅዳል። የቨርጂኒያ ኮድ፣ § 22.1-214 C.

## ለፍትህ ሂደት ጥያቄ ማቅረብ

**የፍትህ ሂደት ጥያቄዎ የተወሰኑ መረጃዎችን ማካተት አለበት። ጥያቄዎትን በሚስጢር እንዲያዝ የመጠየቅ መብት አልዎት። ለጥያቄዎ ምላሽ የማግኘት መብት አልዎት።**

### አጠቃላይ

ችሎት ለመጠየቅ፣ እርስዎ ወይም የትምህርት ዲቪዥኑ (ወይም የእርስዎ ወይም የትምህርት ዲቪዥኑ ጠበቃ) የፍትህ ሂደት ጥያቄ ለሌላኛው አካል ማቅረብ አለበት። ያ የፍትህ ሂደት ችሎት ጥያቄ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሁሉንም ይዘቶች ማካተት እና በሚስጥር መያዝ አለበት።

እርስዎ ወይም የትምህርት ዲቪዥኑ፣የችሎት ጥያቄ ያቀረበው አካል የጥያቄውን ቅጂ ለቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) ማቅረብ አለበት።

### የጥያቄው ይዘት

የፍትህ ሂደት ችሎት ጥያቄው የሚከተሉትን ማካተት አለበት:-

1. የተማሪው ስም
2. የተማሪው የመኖሪያ አድራሻ
3. የተማሪው የትምህርት ቤት አድራሻ
4. ተማሪው ቤት አልባ ልጅ ወይም ወጣት ከሆነ፣ የተማሪው የአድራሻ መረጃ እና የትምህርት ቤት ስም

5. ከችግሩ ጋር የተያያዙ እውነታዎችን ጨምሮ ከታቀደው ወይም ከተከለከለው ተግባር ጋር በተገኛኘ የችግሩ ተፈጥሮ መግለጫ፣ **እና**

6. በወቅቱ የታወቁ፣ ለእርስዎ ወይም ለዲቪዥኑ የተገኙ የችግሩ መፍትሄ።

እርስዎ ወይም የትምህርት ዲቪዥኑ (ወይም የእርስዎ ወይም የትምህርት ዲቪዥኑ ጠበቃ) ከላይ የተዘረዘሩትን መረጃዎች ያካተተ የፍትህ ሂደት ጥያቄ እስካላቀረቡ ድረስ እርስዎ ወይም የትምህርት ዲቭዥኑ የፍትህ ሂደት ችሎት ላይኖርዎት ይችላል።

### የፍትህ ሂደት ጥያቄው በቂነት

የፍትህ ሂደቱ ወደፊት እንዲቀጥል ጥያቄው በቂ ነው ተብሎ መታሰብ አለበት። የፍትህ ሂደት ጥያቄው የተቀበለው አካል (እርስዎ ወይም የትምህርት ዲቪዥኑ) በ15 የቀን መቁጠሪያ ጥያቄውን ከበተቀበሉበት ቀናት ውስጥ ለችሎት ሹሙ (አፊሰሩ) እና ለሌላኛው አካል በጽሁፍ የፍትህ ሂደት ጥያቄው ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች አያሟላም ብሎ ካላሳወቁ በስተቀር የፍትህ ሂደት ጥያቄው በቂ ነው ተብሎ ታሳቢ ይደረጋል (ከላይ ያሉትን የይዘት መስፈርቶች እንዳሟላ ይቆጠራል)።

ማሳወቂያው በደረሰው በ5 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ ተቀባዩ አካል (እርስዎ ወይም የትምህርት ዲቪዥኑ) የፍትህ ሂደት ጥያቄ በቂ እንዳልሆነ ከተገነዘቡ፣ የችሎቱ ሹሙ የፍትህ ሂደት ጥያቄው ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ይወስን እና እርስዎን እና የትምህርት ዲቪዥኑን ወድያዉኑ በጽሑፍ ያሳውቃል።

### ለማሻሻያ ጥያቄ ማቅረብ

እርስዎ ወይም የትምህርት ዲቪዥኑ፣ በፍትህ ሂደት ጥያቄ ላይ ለውጦችን ማድረግ የሚችሉት፡-

**1.** ሌላኛው ወገን ለውጦቹን በጽሁፍ ሲያጸድቅ እና የፍትህ ሂደት ጥያቄን ከዚህ በታች በተገለፀው የመፍትሄ ስብሰባ ለመፍታት እድሉ ሲሰጣቸው፣ ***ወይም***

2. የፍትህ ሂደት ችሎቱ ከመጀመሩ ከ 5 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ፣ የችሎት ሹሙ ለለውጦቹ ፈቃድ ሲሰጣቸው ብቻ ነው።

ጠያቂው አካል (እርስዎ ወይም የትምህርት ዲቪዥኑ) በፍትህ ሂደት ጥያቄ ላይ ለውጦች ካደረጉ፣ የመፍትሄው ስብሰባ የጊዜ ሰሌዳዎች (ጥያቄው በደረሰው በ15 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ) እና የመፍትሄው ጊዜ (ጥያቄው በደረሰ በ30 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ) የተሻሻለው ጥያቄ በቀረበበት ቀን እንደገና ይጀምራሉ።

### የትምህርት ዲቪዥን ለፍትህ ሂደት ጥያቄ የሰጠው ምላሽ

***በቅድመ ጽሁፍ ማሳወቂያ*** ስር እንደተገለጸው፣ የትምህርት ዲቪዥኑ የፍትህ ሂደት ጥያቄዎን በተመለከተ ቀደም ብሎ የጽሁፍ ማወቂያ ካልላከልዎት፣ የትምህርት ዲቪዥኑ የፍትህ ሂደት ጥያቄ በደረሰው በ10 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ የሚከተሉትን ያካተተ ምላሽ መላክ አለበት።

1. የትምህርት ዲቪዥኑ የፍትህ ሂደት ጥያቄ ላይ የተነሳውን እርምጃ ለመውሰድ ለምን እንዳቀረበ ወይም እንዳልተቀበለ የሚገልጽ ማብራሪያ፤
2. የልጅዎ የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን ግምት ውስጥ ያስገቡዋቸው ሌሎች አማራጮች መግለጫ እና እነዚያ አማራጮች ውድቅ የተደረጉባቸው ምክንያቶች፤
3. የእያንዳንዱ የግምገማ ሂደት፣ ምዘና፣ መዝገብ፣ ወይም የትምህርት ዲቪዥኑ ለታቀደው ወይም ውድቅ ለተደረገው እርምጃ መሰረት ሆኖ ያገለገለውን ሪፖርት መግለጫ፣ **እና**

4. ከትምህርት ዲቪዥኑ የታቀደ ወይም ውድቅ የሆነ ድርጊት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የሌሎች ምክንያቶች መግለጫ።

ከላይ ከቁጥር 1-4 የተጠቀሱት መረጃ የትምህርት ዲቪዥኑ መስጠቱ፣ እርስዎ ያቀረቡት የፍትህ ሂደት ጥያቄ በቂ አለመሆኑን ከማረጋገጥ አያግደውም።

**ለፍትህ ሂደት ጥያቄ የሌላ ወገን ምላሽ**

***የትምህርት ዲቪዥን ለፍትህ ሂደት ጥያቄ የሰጠው ምላሽ*** በሚለው ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ንዑስ ርእስ ስር ከተገለጸው በቀር፣ የፍትህ ሂደት ጥያቄ የሚቀበለው አካል ቅሬታው በደረሰው በ10 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ፣ ለሌላኛው ወገን በጥያቄው ውስጥ ለተነሱ ጉዳዮች የሚዳስስ ምላሽ መላክ አለበት።

## የሞዴል ቅጾች

**የፍትህ ሂደትን ለመጠየቅ እንዲረዳዎ የሞዴል ቅጾችን የመጠቀም መብት አልዎት።**

የፍትህ ሂደት እና የስቴት ቅሬታ ለማቅረብ እንዲረዳዎት የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) የሞዴል ቅጾችን ማዘጋጀት አለበት። ሆኖም፣ የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) ወይም የትምህርት ዲቪዥኑ እነዚህ የሞዴል ቅጾችን እንዲጠቀሙ ላያስገድድ ይችላል። በእርግጥ፣ የፍትህ ሂደት ወይም የስቴት ቅሬታ ለማቅረብ አስፈላጊውን መረጃ እስካካተተ ድረስ ይህን ቅጽ ወይም ሌላ ተገቢ የሞዴል ቅጽ መጠቀም ይችላሉ። የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) ሞዴል ቅጹ በ https://www.doe.virginia.gov/?navid=652 ላይ ይገኛል።

## የፍትህ ሂደት ችሎት በመጠባበቅ ላይ የተማሪ ምደባ

**ልዩ ከሆኑ ሁኔታዎች በስተቀር፣ እርስዎ እና የትምህርት ዲቪዥኑ የተለየ ስምምነት እስካላደረጋችሁ ድረስ፣ የፍትህ ሂደቱ መፍትሄ እስኪያገኝ ድረስ ልጅዎ ተመሳሳይ የትምህርት አገልግሎቶችን እያገኘ የመቀጠል መብት አለው።**

***የአካል ጉዳተኛ ልጆችን ስነ-ምግባር ለማስጠበቅ የሚውል አሰራር*** በሚለው ርዕስ ሥር ከተገለጹት በቀር፣ የፍትህ ሂደት ጥያቄ አንድ ጊዜ ለሌላኛው ወገን ከተላከ፣ በመፍትሄ ሂደቱ ጊዜ እና ማንኛውንም የማያዳላ የፍትህ ሂደት ችሎት ወይም የፍርድ ቤት ሂደት ውሳኔን በመጠባበቅ ላይ እያለ፣ እርስዎ እና የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) ወይም የትምህርት ዲቪዥኑ በተቃራኒው ካልተስማሙ በስተቀር ልጅዎ አሁን ባለው የትምህርት ምደባ ውስጥ መቆየት አለበት።

የፍትህ ሂደቱ ወደ የህዝብ ትምህርት ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የመግባት ጥያቄን የሚያካትት ከሆነ፣ ልጅዎ በእርስዎ ፍቃድ፣ እነዚህ ሂደቶች እስኪጠናቀቁ ድረስ በመደበኛው የህዝብ ትምህርት ቤት ፕሮግራም ውስጥ መግባት አለበት።

የፍትህ ሂደት ችሎት ጥያቄ በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ክፍል B ስር የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎቶች መስጠትን የሚያካትት ከሆነ፣ በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ክፍል C ስር ከማገልገል ወደ በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ክፍል B ለሚሸጋገር እና ለክፍል C አገልግሎት ብቁ ላልሆነው እና ሶስት አመት ለሞላው ልጅዎ፣ የትምህርት ዲቪዥኑ እሱ ወይም እሷ ሲቀበሉት የነበረዉን ክፍል C አገልግሎቶችን እንዲሰጥ አይገደድም።

ልጁ በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ክፍል B መሰረት ብቁ ሆኖ ከተገኘ እና ልጅዎ የልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲያገኝ ከፈቀዱ፣የችሎቱን ውጤት በመጠባበቅ ላይ እያሉ የትምህርት ዲቪዥኑ እነዚያን አካራካሪ ያልሆኑትን (እርስዎ እና የትምህርት ዲቪዥኑ ሁለታችሁም የተስማማችሁበትን) የልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን መስጠት አለበት። ክፍል C ከጨቅላ ህጻናት እና ታዳጊዎች ጋር የሚገናኙ የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ክፍል ነው። በቨርጂኒያ፣ አካል ጉዳተኛ ልጆች ከ2 እስከ 21 ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ ለክፍል B አገልግሎቶች ብቁ ናቸው።

**የመፍትሄ ሂደት**

**የፍትህ ሂደት ችሎት ከመካሄዱ በፊት፣ በፍትህ ሂደት ጉዳይዎ ላይ ስላሉ ችግሮች ለመወያየት እና ስጋቶችዎን ለመፍታት ከትምህርት ቤት ሰራተኞች ጋር የመገናኘት መብት አልዎት። ነገር ግን፣ እርስዎ እና የትምህርት ዲቪዥኑ ሁለታችሁም የመፍትሄ ስብሰባ እንደማትፈልጉ መስማማት፣ ወይም ሁለታችሁም ሽምግልና ለመጠቀም መስማማት ትችላላችሁ።**

**የመፍትሄ ስብሰባ**

የፍትህ ሂደት ጥያቄዎን ማስታወቂያ በደረሰዎት በ15 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ እና የፍትህ ሂደት ችሎቱ ከመጀመሩ በፊት፣ የትምህርት ዲቪዥኑ ከእርስዎ እና ከሚመለከታቸው ለፍትህ ሂደት ባቀረቡት ጥያቄ ላይ የተገለጹትን እውነታዎች ጋር ልዩ እውቀት ካላቸው የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን አባላት ጋር ስብሰባ መጥራት አለበት።

ስብሰባው:-

1. የትምህርት ዲቪዥኑ ወክሎ የመወሰን ስልጣን ያለው የትምህርት ዲቪዥኑ ተወካይ ማካተት አለበት፤ <u>**እና**</u>
2. እርስዎ ከጠበቃ ጋር ካልሄዱ በስተቀር፣ የትምህርት ዲቪዥኑን ጠበቃ ላይካተት ይችላል።

የስብሰባው አላማ እርስዎ የፍትህ ሂደት ጥያቄዎን እና የጥያቄውን መሰረት በሆኑት እውነታዎች ላይ እንዲወያዩ ሲሆን ይህም የትምህርት ዲቪዥኑን አለመግባባቱን የመፍታት እድል እንዲኖረው ያደርጋል።

የመፍትሄ ስብሰባው አስፈላጊ የማይሆነው:-

1. እርስዎ እና የትምህርት ዲቪዥኑ ስብሰባዉን ለማስቀረት በጽሁፍ ከተስማሙ፣ <u>**ወይም**</u>
2. እርስዎ እና የትምህርት ዲቪዥኑ **ሽምግልና** በሚለው ርዕስ እንደተገለጸው የሽምግልና ሂደቱን ለመጠቀም ከተስማሙ ነው።

**የመፍትሄ ጊዜ**

የፍትህ ሂደት ጥያቄዎ በደረሰው በ30 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ የትምህርት ዲቪዥኑ የፍትህ ሂደት ጥያቄውን እርስዎን ባረካ መንገድ ካልፈታው (በመፍትሄ ሂደቱ ጊዜ ውስጥ) የፍትህ ሂደት ችሎቱ ሊካሄድ ይችላል።

የመጨረሻውን የፍትህ ሂደት ውሳኔ ለመስጠት የ45 ተከታታይ ቀናቱ የጊዜ ሰሌዳ የሚጀምረው፣ ከዚህ በታች እንደተገለጸው በ30-የቀን መቁጠሪያው የመፍትሄ ጊዜ ላይ ከተደረጉት ማስተካከያዎች በስተቀር፣ የ30-ቀን የቀን መቁጠሪያው የመፍትሄ ጊዜ ሲያልቅ ነው።

እርስዎ እና የትምህርት ዲቪዥኑ ሁለታችሁም የመፍትሄ ሂደቱን ለመተው ወይም ሽምግልናን ለመጠቀም ካልተስማማችሁ በስተቀር፣ በስብሰባ ላይ ለመሳተፍ እስክትስማሙ ድረስ፣ በመፍትሄ ስብሰባው ላይ አለመሳተፍዎ የመፍትሄ ሂደቱን እና የፍትህ ሂደት ችሎቱን ጊዜ ያዘገየዋል።

ምክንያታዊ ጥረቶችን ካደረጉ እና እነዚህን ጥረቶች ከመዘገቡ በኋላ፣ የትምህርት ዲቪዥኑ በመፍትሄ ስብሰባው ላይ የእርስዎን ተሳትፎዎ ማግኘት ካልቻለ፣ የትምህርት ዲቪዥኑ በ30-ቀን የቀን መቁጠሪያ የመፍትሄ ጊዜ ማብቂያ ላይ፣ የችሎት ሹሙ የእርስዎን የፍትህ ሂደት ጥያቄ ውድቅ እንዲያረግብዎት ሊጠይቅ ይችላል። የእንደዚህ አይነት ጥረቶች ሰነዶች መዝገብ፣ የትምህርት ዲቪዥኑ በጋራ ስምምነት ላይ የተመሰረተ ጊዜ እና ቦታን ለማዘጋጀት ያደረጋቸውን ሙከራዎች ማካተት አለበት፤ ለምሳሌ፡-

- የተደረጉ ወይም የተሞከሩ የስልክ ጥሪዎች እና የጥሪዎቹ ውጤቶች ዝርዝር መዛግብት፤
- ወደ እርስዎ የተላኩ የደብዳቤ ቅጂዎች እና ማንኛውም የተገኙ ምላሾች፤ እና
- ወደ ቤትዎ ወይም ወደ ሥራ ቦታዎ የተደረጉ ጉብኝቶች ዝርዝር መዛግብት እና የእነዚያ ጉብኝቶች ውጤቶች።

የትምህርት ዲቪዥኑ የፍትህ ሂደት ጥያቄዎን በደረሰው በ15 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ የመፍትሄ ስብሰባውን ማካሄድ ካልቻለ <u>**ወይም**</u> የመፍትሄ ስብሰባው ላይ ካልተሳተፈ፣ የችሎት ሹሙ የ45 ተከታታይ ቀናት የፍትህ ሂደት ችሎት የጊዜ ሰሌዳ እንዲጀምር ትእዛዝ እንዲሰጥ መጠየቅ ይችላሉ።

### በ30 ተከታታይ ቀናት የመፍትሄ ጊዜ ላይ ማስተካከያዎች

እርስዎ እና የትምህርት ዲቪዥኑ የመፍትሄውን ስብሰባ ለመተው በጽሁፍ ከተስማሙ፣ የ45- የቀን መቁጠሪያ-ቀን የፍትህ ሂደት ችሎት የጊዜ ሰሌዳ በሚቀጥለው ቀን ይጀምራል።

ሽምግልና ወይም የመፍትሄ ስብሰባው ከተጀመረ በኋላ እና የ30 ተከታታይ ቀናቱ የመፍትሄ ጊዜ ከማብቃቱ በፊት እርስዎ እና የትምህርት ቤቱ ዲቪዥን ምንም አይነት ስምምነት ሊኖር እንደማይችል በጽሁፍ ከተስማማችሁ፣ለፍትህ ሂደቱ የ45 ተከታታይ ቀናት የጊዜ ሰሌዳ ችሎት በሚቀጥለው ቀን ይጀምራል።

እርስዎ እና የትምህርት ዲቪዥኑ የሽምግልና ሂደቱን ለመጠቀም ከተስማሙ፣ የ30-ቀን የቀን መቁጠሪያው የመፍትሄ ጊዜ ሲያበቃ ሁለቱም ወገኖች ስምምነት ላይ እስኪደርሱ ድረስ ሽምግልናውን ለመቀጠል በጽሁፍ መስማማት ይችላሉ። ነገር ግን፣ እርስዎ ወይም የትምህርት ዲቪዥኑ ከሽምግልና ሂደት ከወጡ፣ የ45 ተከታታይ ቀናቱ የፍትህ ሂደት ችሎት የጊዜ ሰሌዳ በሚቀጥለው ቀን ይጀምራል።

### የጽሑፍ ስምምነት ውል

በመፍትሄው ስብሰባ ላይ አለመግባባቱን ለመፍታት ከተወሰነ፣ እርስዎ እና የትምህርት ዲቪዥኑ ህጋዊ አስገዳጅ የስምምነት ውል ማድረግ አለባችሁ፡-

1. በእርስዎ እና የትምህርት ዲቪዥኑን የማስገደድ ስልጣን ባለው የትምህርት ዲቪዥኑ ተወካይ የተፈረመ፣ <u>**እና**</u>
2. በማንኛውም የስቴት ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት (ይህን አይነት ጉዳይ የማየት ስልጣን ያለው የስቴት ፍርድ ቤት) ወይም በፌደራል ዲስተሪክት ፍርድ ቤት ተፈጻሚ የሚሆን ይሆናል።

**የስምምነት ግምገማ ጊዜ**

እርስዎ እና የትምህርት ዲቪዥኑ በመፍትሄ ስብሰባው ምክንያት ስምምነት ላይ ከደረሱ፣ እርስዎ እና የትምህርት ዲቪዥኑ፣ ስምምነቱን በተፈራረሙበት በ3 የስራ ቀናት ውስጥ የትኛውም ወገን (እርስዎ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲቪዥን) ስምምነቱን ሊያፈርሱ ይችላሉ።

## የማያዳላ የፍትህ ሂደት ችሎት

---

> ***በትምህርት ቤት ዲቪዥኑ ወይም በቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ ተቀጥሮ በማይሰራ እና እውቀት ባለው የችሎት ሹም የፍትህ ሂደት ችሎት የማግኘት መብት አልዎት። እርስዎ እና የትምህርት ዲቪዥኑ የፍትህ ሂደት ችሎቶች ህጎች እና የጊዜ ሰሌዳዎችን መከተል አለባችሁ።***

**አጠቃላይ**

በማንኛውም ጊዜ የፍትህ ሂደት ጥያቄ በቀረበ ጊዜ እርስዎ ወይም በክርክሩ ውስጥ የተሳተፈው የትምህርት ዲቪዥኑ፣ ***የፍትህ ሂደት ጥያቄ እና የመፍትሄ ሂደት*** ክፍሎች ላይ እንደተገለጸው፣ የማያዳላ የፍትህ ሂደት ችሎት የማግኘት እድል ሊኖራችሁ ይገባል።

**የማያዳላ የችሎት ሹም**

የችሎት ሹም ቢያንስ፡-

1. በልጁ ትምህርት ወይም እንክብካቤ ላይ ተሳተፈ የሆነውን የትምህርት ዲቪዥን ወይም የVDOE ሰራተኛ መሆን የለበትም። ነገር ግን፣ አንድ ሰው ኤጀንሲው በዋናነት እንደ የችሎት ሹም ሆነው እንዲያገለግሉ የሚከፍላቸው በመሆኑ ብቻ የኤጀንሲው ተቀጣሪ ናቸው ማለት አይደለም።

2. የችሎቱ ሹም በችሎቱ ሂደት ተጨባጭነት ጋር የሚጋጭ የግል ወይም ሙያዊ ፍላጎት ሊኖረው አይገባም።

3. እውቀት ያለውና የበአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) አቅርቦት፣ የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌን (IDEA) የሚመለከቱት የፌደራል እና የስቴት ደንቦችን እና በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌን (IDEA) በፌዴራል እና በስቴት ፍርድ ቤቶች የሚሰጠውን የህግ ትርጉም የሚረዳ መሆን አለበት፤ እና

4. ከተገቢው መደበኛ የህግ አሠራር ጋር፣ ችሎቶችን ለማካሄድ፣ ውሳኔዎችን የመወሰን እና የመጻፍ እውቀት እና ችሎታ ሊኖረው ይገባል።

እያንዳንዱ የትምህርት ዲቪዥን፣ የእያንዳንዱን ችሎት ሹም ብቃት መግለጫ ያካተተ እንደ ችሎት ሹሞች የሚያገለግሉትን የስም ዝርዝር መያዝ አለበት። ይህ መረጃ በቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) ድህረ-ገጽ ላይ ወይም የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያን (VDOE) በማነጋገርም ይገኛል።

**የፍትህ ሂደት ችሎት ርዕሰ ጉዳይ**

የልዩ ትምህርት የችሎት ሹም፣ ከተወሰኑ እውነታዎች እና ሁኔታዎች አንጻር ችሎቱን የጠየቀው አካል በማሳወቂያው ላይ ያልተነሱ ጉዳዮችን በሁለቱም ወገኖች በችሎቱ ላይ እንዲያነሳ የመፍቀድ ስልጣን አለው። ይህ ማለት በተግባር :-

የፍትህ ሂደት ችሎት የጠየቀ አካል (እርስዎ ወይም የትምህርት ዲቪዥን) የችሎቱ ጥያቄ አካል ያልሆኑትን ተጨማሪ ጉዳዮችን በችሎቱ ጊዜ የማንሳት ሙሉ መብት የላቸውም። ችሎቱን የሚጠይቀው አካል በችሎቱ ላይ ተጨማሪ ጉዳዮችን ሊያነሳ የሚችለው፣ ከሚከተሉት በስተቀር፣ ሌላኛው ወገን ከተስማማ ብቻ ነው።

በሚሰሙት ተጨማሪ ጉዳዮች ላይ ሌላኛው ወገን ካልተስማማ፣ ችሎቱን የሚጠይቀው አካል ተጨማሪ ጉዳዮች ላይ ለብቻው እንዲታይ ሌላ የፍትህ ሂደት ችሎት ጥያቄ ማቅረብ አለበት።

ችሎቱን የሚጠይቀው አካል በሌላኛው ወገን ለተነሱት እውነታዎች፣ ጉዳዮች ወይም ክርክሮች *ምላሽ ለመስጠት* ተጨማሪ ጉዳዮችን እንዲያካትት የችሎቱን ሹም ከጠየቀ፣ ሌላኛው ወገን ባይስማማም የችሎቱ ሹም የጠየቀውን አካል በችሎቱ ላይ ተጨማሪ ጉዳዮች እንዲያነሳ የመፍቀድ ሥልጣን አለው።

## የችሎት መብቶች

**በፍትህ ሂደት ባሉ ችሎቶች ላይ አንዳንድ መብቶች አሉዎት፤ ከችሎቱ በፊት፣ ትምህርት ቤቱ በችሎቱ ወቅት የሚጠቀምባቸውን ሁሉንም ማስረጃዎች የማግኘት መብትን ጨምሮ፣ ጠበቃ ወይም ሌሎች የሚረዷችሁ ሰዎች፣ ያለ ምንም ወጪ የችሎቱ የማህደር ቅጂ የማግኘት እንዲሁም ችሎቱ ለህዝብ ክፍት እንዲሆን የማድረግ መብት አልዎት።**

### አጠቃላይ

ማንኛውም የፍትህ ሂደት ችሎት አካል (ከስነ ምግባር ማስጠበቅ አሰራር ጋር የተያያዘ ችሎትን ጨምሮ) የሚከተሉትን የማድረግ መብት አልዋቸው:-

1. የአካል ጉዳተኛ ልጆችን ችግር በተመለከተ ከጠበቃ እና/ወይም ልዩ እውቀት ወይም ስልጠና ካላቸው ሰዎች ጋር መቅረብ እና ማማከር፤
2. ማስረጃ የማቅረብ እና ፊት ለፊት የመጋፈጥ፣ የመመርመር እና እንደግዴታ ምስክሮች እንዲቀርቡ የመጠየቅ፤
3. ችሎቱ ከመድረሱ ከአምስት (5) የስራ ቀናት በፊት ለችሎቱ ወገኖች ያልተገለፀውን ማንኛውንም ማስረጃ በችሎቱ ላይ ማስተዋወቅን የችሎቱ ሹም እንዲከለክል የመጠየቅ፤
4. የችሎቱን የጽሑፍ፣ ወይም በእርስዎ ምርጫ፣ ኤሌክትሮኒካዊ፣ የቃል በ ቃል የማህደር ቅጂ የማግኘት፤ እና
5. በጽሁፍ ወይም በእርስዎ ምርጫ የኤሌክትሮኒካዊ የእውነት ግኝቶችን እና ውሳኔዎችን የማግኘት።

### ተጨማሪ መረጃን ይፋ ማድረግ

የፍትህ ሂደት ችሎቱ ከመካሄዱ ቢያንስ ከአምስት (5) የስራ ቀናት በፊት፣ እርስዎ እና የትምህርት ዲቪዥኑ በዚያ ቀን የተጠናቀቁትን ሁሉንም ግምገማዎች እና እርስዎ ወይም የትምህርት ዲቪዥኑ በችሎቱ ላይ ሊጠቀሙባቸው ያሰቡትን ግምገማዎቹን መሰረት በማድረግ የተሰጡት የውሳኔ ሃሳቦች ለእያንዳንዳችሁ ይፋ ማድረግ አለባችሁ።

የችሎቱ ሹም ይህንን መስፈርት ያላሟላ አካል፣ ከሌላኛው ወገን ፈቃድ ውጭ፣ ተገቢውን ግምገማ ወይም የውሳኔ ሃሳብ በችሎቱ ላይ እንዳያቀርብ ሊከለክል ይችላል።

### በችሎት ላይ የወላጅ መብቶች

የሚከተሉትን የማድረግ መብት **ሊሰጥዎት ይገባል:-**

1. ልጅዎ እንዲገኝ የማድረግ፤
2. ችሎቱን ለህዝብ ክፈት እንዲሆን የማድረግ፤ **እና**
3. የችሎቱን ማህደር የማግኘት፣የእውነታው ግኝቶች እና ውሳኔዎች ያለምንም ክፍያ እንዲሰጥዎት የማድረግ።

## የችሎት ውሳኔዎች

**በእርስዎ የፍትህ ሂደት ጥያቄ ውስጥ ባሉ ጉዳዮች ላይ በመመስረት ውሳኔ የማግኘት፣ አዲስ ጉዳዮች ከተነሱ የተለየ የፍትህ ሂደት ጥያቄ የማቅረብ እና ውሳኔው ለህዝብ ይፋ ከመሆኑ በፊት ልጅዎን ሊገልጹ የሚችሉ መረጃዎች ከችሎቱ ውሳኔ እንዲጠፉ የማግረግ መብት አልዎት።**

የእርስዎ ልጅ ነጻ እና ተገቢ የሆነ የሕዝብ ትምህርት (FAPE) ማግኘቱን በተመለከተ የችሎት ሹሙ ውሳኔ በምክንያት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት። የአሰራር ጥሰትን በሚመለከቱ ጉዳዮች፣ የችሎት ሹም ልጅዎ የነጻ እና ተገቢ የሆነ የሕዝብ ትምህርት (FAPE)ን አለማግኘቱን የሚወስነው፣የአሰራር ጉድለቶቹ:-

1. በልጅዎ የነጻ እና ተገቢ የሆነ የሕዝብ ትምህርት (FAPE) መብት ላይ ጣልቃ ከገቡ፤
2. የልጅዎ የነጻ እና ተገቢ የሆነ የሕዝብ ትምህርት (FAPE) አቅርቦትን በተመለከተ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ የመሳተፍ እድልዎ ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ጣልቃ ከገቡ፤ **<u>ወይም</u>**
3. የትምህርት ጥቅማጥቅሞችን ማጣት ምክንያት ከሆኑ ብቻ ነው።

### ማስታወሻ

ከላይ ከተገለጹት ማናቸውም ድንጋጌዎች ቢሆኑ፣ አንዳቸውም የችሎት ሹሙ የትምህርት ዲቪዥኑን የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) (34 CFR §§300.500 እስከ 300.536) ስር የፌዴራል ደንቦች የአሰራር ከለላዎች ክፍል ውስጥ የተቀመጡትን መስፈርቶች እንዲያከብሩ ትዕዛዝ ከመስጠት አያግዳቸውም ።

### የተለየ የፍትህ ሂደት ችሎት ጥያቄ

በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ክፍል B (34 CFR §§300.500 እስከ 300.536) ስር ባለው የፌደራል ደንቦች የአሰራር ከለላዎች ክፍል ውስጥ አስቀድሞ በተመለከተው የፍትህ ሂደት ጥያቄ በተለየ ጉዳይ ላይ የተለየ የፍትህ ሂደት ጥያቄ እንዳያቀርቡ የሚያግድ ትርጉም ሊሰጠው የሚችል ምንም ደንብ የለም።

### ግኝቶች እና ውሳኔዎች ለቨርጂኒያ ስቴት የልዩ ትምህርት አማካሪ ኮሚቴ እና አጠቃላይ ህዝብ ማቅረብ

የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE)፣ ማንኛውንም የግል ማንነት የሚገልጽ መረጃን የመሰረዝ እንዲሁም:-

1. በፍትህ ሂደት ችሎት የተገኙ ግኝቶችን እና ውሳኔዎችን ለስቴቱ የልዩ ትምህርት አማካሪ ኮሚቴ የማቅረብ፣ <u>እና</u>
2. እነዚያን ግኝቶች እና ውሳኔዎች ለህዝብ ተደራሽ የማድረግ ሃላፊነት አለው።

የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) እነዚህ ውሳኔዎችን በየሩብ ዓመቱ በድህረ-ገጹ ላይ በመለጠፍ ኃላፊነቱን ያሟላል።

## የችሎት እና ግምገማዎች የጊዜ ሰሌዳዎች እና አመቺነት

**ችሎቱ ለእርስዎ በሚመች ጊዜ እና ቦታ የማግኘት፣ በችሎቱ ላይ በተወሰነ የጊዜ ሰሌዳ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የማግኘት እና የውሳኔውን ግልባጭ የማግኘት መብት አልዎት።**

የ30-ቀን የመፍትሄ ስብሰባ መቁጠሪያው ጊዜ ካለፈ በኋላ፣ ከ45 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ***<u>ወይም</u> የ30 የቀን መቁጠሪያ-ቀን የመፍትሄ ጊዜ ማስተካከያ*** በሚለው ንዑስ ርእስ ስር እንደተገለጸው፣ከተስተካከለው የጊዜ ማብቂያ ጊዜ ከ45 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ

የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) የሚከተሉትን መደረጋቸውን ማረጋገጥ አለበት።

1. በችሎቱ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ላይ መደረሱ፤ <u>**እና**</u>
2. የውሳኔው ግልባጭ ለእያንዳንዱ ወገን በፖስታ መላኩ።

የችሎቱ ሹም፣ አንዳቸውም ወገኖች ከላይ ከተገለጸው የ45 ተከታታይ ቀናት ጊዜ በላይ የጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ ካቀረቡ፣ ጥያቃቸውን ተቀብሎ የተወሰነ ማራዘሚያ ሊሰጥ ይችላል።በተጨማሪ የችሎት ሹሙ ለልጁ የሚጠቅም ከሆነ ብቻ ማራዘሚያውን እንዲሰጥ የቨርጂኒያ ህግጋት ያስገድዳል።

እያንዳንዱ ችሎት ለእርስዎ እና ለልጅዎ በምክንያታዊ ምቹ በሆነ ጊዜ እና ቦታ መከናወን አለበት።

## የፍትሐ ብሄር ክሶች እና ክሶቹ የሚመሰረቱበት የጊዜ ገደብ

**እርስዎ ወይም የትምህርት ዲቪዥኑ በችሎቱ ውሳኔ ካልተስማማችሁ፣ የፍትሐ ብሔር ክስ በስቴት ወይም በፌደራል ፍርድ ቤት ልታቀርቡ ትችላላችሁ፤ ነገር ግን የጊዜ ገደብ አለው።**

### አጠቃላይ

ማንኛውም አካል (እርስዎ ወይም የትምህርት ዲቪዥኑ) በፍትህ ሂደት ችሎት ግኝቶች እና ውሳኔዎች (ከስነ ምግባር ለማስጠበቅ የሚውል አሰራሮች ጋር የተያያዘ ችሎትን ጨምሮ) ያልተስማሙ ወገኖች በጉዳዩ ላይ የፍትሐ ብሔር ክስ የማቅረብ መብት አላቸው። ክሱ፣ ክርክር ውስጥ ያለውን መጠን ግምት ውስጥ ሳያስገባ፣ በቨርጂኒያ ፍርድ ቤት ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት (ይህን አይነት ጉዳይ የማየት ስልጣን ያለው የስቴት ፍርድ ቤት) ወይም በፌዴራል ዲስትሪክት ፍርድ ቤት ሊቀርብ ይችላል።

### የጊዜ ገደብ

ድርጊቱን የሚያመጣው ወገን (እርስዎ ወይም የትምህርት ዲቪዥኑ) የችሎት ሹሙ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን አንሥቶ፣ የፍትሐ ብሔር ክስ በፌዴራል ዲስትሪክት ፍርድ ቤት ለመቅረብ 90 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ይኖረዋል ወይም በ180 ቀናት ውስጥ የስቴት ፍርድ ቤት ላይ ማቅረብ ይኖርበታል።

### ተጨማሪ ሂደቶች

በማንኛውም የፍትሐ ብሔር ክስ፣ ፍርድ ቤቱ:-

1. የአስተዳደር ሂደቶችን መዝገቦችን ይቀበላል፤
2. በጥያቄዎ ወይም በትምህርት ቤቱ ዲቪዥን ጥያቄ ተጨማሪ ማስረጃዎችን ይሰማል፤ <u>**እና**</u>
3. ውሳኔውን በማስረጃዎች ብዛት ላይ በመመስረት ፍርድ ቤቱ ተገቢ ነው ብሎ ያመነበትን የዳኝነት ውሳኔ ይሰጣል።

### የፌዴራል ዲስትሪክት ፍርድ ቤቶች ሥልጣን

የፌደራል ዲስትሪክት ፍርድ ቤቶች በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ስር በሚደረጉ ክሶች ላይ የክርክር መጠንን ከግምት ውስጥ ሳያስገባ የመወሰን ስልጣን አላቸው።

**ማስታወሻ**

በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) በክፍል B የተጻፈ ማናቸውም ቢሆን፣ በዩናይትድ ስቴትስ ሕገ-መንግሥት፣ በ1990 በወጣው አሜሪካንስ ዊዝ ዲዝአቢሊቲስ ድንጋጌ፣ በ1973 በወጣው ሪሐቢሊቴሽን ድንጋጌ በክፍል V (ክፍል 504) ወይም የአካል ጉዳተኛ ሕጻናትን መብቶች ለማስጠበቅ በወጡ የፌዴራል ሕግጋት ሥር ያሉ መብቶችን፣ አካሄድን እና መፍትሔዎችን ከመጠቀም የሚያግድ ወይም የሚገድብ አይሆንም፤ ሆኖም ግን በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) በክፍል B ስር የዳኝነት ውሳኔ ሊሰጥበት በሚችል ጉዳይ ላይ የፍትሐ ብሔር ክስ ከመመስረት በፊት፣ በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) በክፍል B መፍትሔ ሊገኝ እስከሚችልበት መጠን ከላይ የተለገጹት የፍትህ ሂደቶች ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚ መደረግ አለባቸው።

ይህ ማለት በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ስር ከሚገኙት ጋር በተደራረቡ ሌሎች ህጎች ስር የሚገኙ መፍትሄዎች ሊኖሩዎት ይችላሉ ነገርግን በአጠቃላይ በሌሎች ህጎች ስር እፎይታ ለማግኘት በቀጥታ ወደ ፍርድ ቤት ከመሄዱ በፊት በመጀመሪያ በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ስር ያሉትን አስተዳደራዊ መፍትሄዎች (ማለትም የፍትህ ሂደት ችሎት ሂደቶችን) መጠቀም አለብዎት ማለት ነው።

**የጠበቃ ክፍያዎች**

---

**ፍርድ ቤት የተሸነፈው አካል የሌላውን አካል ህጋዊ ክፍያዎች መክፈል እንዳለበት ሊወስን ይችላል።**

**አጠቃላይ**

በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ስር በቀረበ ማንኛውም ክስ ወይም ችሎት፣ እርስዎ አሸናፊ ከሆኑ፣ ፍርድ ቤቱ በራሱ ውሳኔ፣ ተገቢ ነው እንደሚለው ምክንያታዊ የሆነ የጠበቃ ክፍያ ሊወስንልዎም ይችላል።

በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ስር በሚቀርብ ማንኛውም ክስ ወይም ችሎት፣ የእርስዎ ጠበቃ ከዚህ የሚከተሉትን የፈጸመ እንደሆነ፣ ፍርድ ቤቱ በራሱ ውሳኔ የእርስዎ ጠበቃ የሚከፍለው ምክንያታዊ የሆኑ የጠበቆች ክፍያን እንደ ወጭው አካል ክርክሩ ላሸነፈው አካል የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) ወይም የትምህርት ዲቪዥኑ ሊወስን ይችላል፡- (ሀ) ያቀረበው ቅሬታ ወይም ክስ ቁም ነገር የሌለው፣ ምንያታዊ ያልሆነ ወይም መሠረት የሌለው ነው ብሎ ፍርድ ቤቱ ከወሰነ፤ ***ወይም*** (ለ) ክርክሩ ቁም ነገር የሌለው፣ ምክንያታዊ ያልሆነ ወይም መሠረት የሌለው መሆኑ በግልጽ እየታየ እንኳን የእርስዎ ጠበቃ ክርክሩን ከቀጠለ፤ ***ወይም***

በማናቸውም የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ስር በቀረበ ክስ ወይም የዳኝነት ችሎት፣ የፍትህ ሂደት ችሎት ወይም ከዚያ በኋላ ደግሞ የፍርድ ቤት ክስ ያቀረቡት ለማናቸውም አግባብነት ለሌለው ዓላማ፣ ለምሳሌ አላስፈላጊ ትንኮሳ ለማድረግ፣ አላፈላጊ መዘግየትን ለመፍጠር ወይም የክሱን ወይም የችሎት ወጪ ከፍ ለማድረግ በሚሆንበት ጊዜ፣ ፍርድ ቤቱ ተገቢ ነው እንደሚለውን ክፍያን እንደ ወጭው አካል በክርክሩ አሸናፊ ለሆነው ለቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) ወይም የትምህርት ዲቪዥኑ እርስዎ ወይም የእርስዎ ጠበቃ የምትከፍሉትን ምክንያታዊ የሆኑ የጠበቆች ክፍያ ሊወስንባችሁ ይችላል።

**የክፍያዎች ውሳኔ**

ፍርድ ቤቱ ምክንያታዊ የሆኑ የጠበቆች ክፍያዎችን በሚከተሉት መልኩ ይወስናል፡-

1. የክፍያዎች መጠን ክሱ ወይም ችሎቱ በተመሰረተበት ማሕበረሰብ ውስጥ በተለመደው ዋጋ እና በአገልግሎቱ ዓይነት እና ጥራት መሠረት ሊወሰኑ ይገባል። የተሰጡ ክፍያዎችን ለማስላት ምንም ጉርሻ ወይም ማባዣ መጠቀም አይቻልም።

2. በጽሁፍ የተዘጋጀ የስምምነት ውል ለእርስዎ ከቀረበልዎ በኋላ በማናቸውም በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ስር በተካሄዱት የክስ ወይም ችሎት ላይ ወይም ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ላወጡት ወጪዎች በሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ የክፍያ ወይም የማወራረድ ትዕዛዝ ላይሰጥዎት ይችላል፡-
    a. የስምምነት ውል የቀረበው በፌዴራል የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ፣ በደንብ 68 በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከሆነ ወይም ጉዳዩ የፍትህ ሂደት ችሎት በሚሆን ጊዜ ደግሞ፣ የችሎቱ ሂደት ከመጀመሩ በፊት ከአስር (10) ተከታታይ ቀናት በላይ ሲቀረው በማናቸውም ጊዜ የቀረበልዎት እንደሆነ፤
    b. የቀረበው ውል በአስር (10) ተከታታይ ቀናት ጊዜ ውስጥ ተቀባይነት ያላገኘ እንደሆነ፤ **እና**
    c. እርስዎ መጨረሻ ላይ የሚያገኙት የዳኝነት ውሳኔ ከቀረበልዎ የስምምነት ውል በላይ ሊሆን አይችልም በማለት ፍርድ ቤቱ ወይም የችሎት ሹሙ የወሰነ እንደሆነ።

   እነዚህ ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በክርክሩ አሸናፊ ከሆኑ እና ከዚህ ቀደም የቀረበልዎትን የስምምነት ውል አለመቀበልዎ አግባብ እንደነበረ በሚገባ ከተረጋገጠ፣ የጠበቃ ክፍያ እና ተያያዥ ወጪዎች ክፍያዎች እንዲከፈልዎ ሊወሰን ይችላል።

3. ከተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን ጋር ለተካሄደ ማናቸውም ስብሰባ፣ ስብሰባው የተካሄደው በአስተዳደር የችሎት ሂደት ወይም በፍርድ ቤት በተመሠረተ ክስ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ክፍያዎች እንዲከፈሉ ውሳኔ አይሰጥም። በቨርጂኒያ፣ ይህ የፍትህ ሂደት ጥያቄ ከማቅረቡ በፊት የሚደረግ ሽምግልናም ያካትታል።

   የመፍትሄ ስብሰባ፣ ***በመፍትሄ ስብሰባ*** ርዕስ ስር እንደተገለጸው፣ በፍትህ ሂደት ችሎት ወይም በፍርድ ቤት ክስ ምክንያት እንደ ተጠራ ስብሰባ ተደርጎ አይቆጠርም፤ እንዲሁም ለእነዚህ ጠበቆች ክፍያ ድንጋጌዎች ሲባል እንደ የፍትህ ሂደት ችሎት ወይም የፍርድ ቤት ክስ አይቆጠርም።

ፍርድ ቤቱ ከዚህ የሚከተሉትን ሲያረጋግጥ፣ በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) በክፍል B ስር የተወሰነውን የጠበቃ ክፍያ እንደአግባብነቱ መጠኑ እንዲቀንስ ሊያደርግ ይችላል፡-

1. እርስዎ ወይም ጠበቃዎ ክሱ ወይም ችሎቱ እየተካሄደ ባለበት ጊዜ፣ የአለመግባባቱ የመጨረሻ መፍትሄ የማግኘቱን ነገር ምክንያታዊ ባልሆነ ሁኔታ ያዘገያችሁ እንደሆነ፤
2. በሌላ መልኩ የክፍያው መጠን በማሕበረሰቡ ተመሳሳይ ክህሎት፣ ዝና እና ልምድ ኖሯቸው ተመሳሳይ አገልግሎት ለሚሰጡ ጠበቆች ከሚከፈለው የሰዓት ክፍያ ምክንያታዊነት በጎደለው ሁኔታ ከፍተኛ ጭማሪ የታየበት እንደሆነ፤
3. የክሱን እና የችሎቱ ሂደት ባሕርይ ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ የተሰጠው አገልግሎት እና ይህም የወሰደው ጊዜ ከሚገባው በላይ ሆኖ ከተገኘ፤ **ወይም**
4. እርስዎን የሚወክለው ጠበቃ ***የፍትህ ሂደት ጥያቄ*** በሚለው ርዕስ ስር እንደተገለጸው የፍትህ ሂደት ጥያቄ ማሳወቂያው ውስጥ ለትምህርት ዲቪዥኑ አግባብነት ያለውን መረጃ ሳይሰጥ የቀረ እንደሆነ።

ሆኖም ግን፣ ስቴቱ ወይም የትምህርት ዲቪዥኑ ምክንያታዊነት በጉደለው ሁኔታ የክሱን ወይም የችሎቱን ሂደት አጓቷል ወይም በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ስር የአሰራር ከለላዎች ድንጋጌዎችን ጥሷል በማለት ፍርድ ቤቱ የወሰነ እንደሆነ፣ የክፍያውን መጠን አይቀንስም።

## የአካል ጉዳተኛ ልጆችን ስነ-ምግባር ለማስጠበቅ የሚውሉ አሰራሮች

**ከልጅዎ ጋር ለተደረጉ የተወሰኑ የስነ ምግባር ማስጠበቂያ እርምጃዎችን ምላሽ የመስጠት መብት አልዎት። ልጅዎ የትምህርት ቤት ህጎችን ከጣሰ፣ የልጅዎ የትምህርት ምደባ ሊቀየር ይችላል። ሆኖም የትምህርት ዲቪዥኑ የተወሰኑ ደረጃዎችን መከተል አለበት።**

### *እያንዳንዱን ጉዳይ በማየት ስለመወሰን*

ከስነ ምግባር ጋር በተገናኘ ለአንድ የትምህርት ቤቱ የተማሪዎች ስነ ምግባር ደንብ የጣሰ የአካል ጉዳተኛ ተማሪ በሚከተሉት መስፈርቶች መሰረት በሚደረገው የምደባ ለውጥ፣ ተገቢ መሆኑን አለመሆኑን ለመወሰን የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች እንደየሁኔታው፣ የተለየ አይነት ሁኔታ ግምት ውስጥ ማስገባት ይችላሉ።

### *አጠቃላይ*

የአካል ጉዳት በሌለባቸውም ልጆች ላይ የሚወስዱት እርምጃ ተመሳሳይ በሆነ መልኩ፣ የትምህርት ቤት ሠራተኞች የስነ ምግባር ደንብን የጣሰ አንድ ተማሪ በወቅቱ ከተመደበበት ተቋም **ከአስር (10)** ***ተከታታይ የትምህርት ቀናት*** ላልበለጠ ጊዜ ወደ ሌላ ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ምድብ ሊያዘዋውሩ፣ ሊቀይሩ ወይም ሊያግዱ ይችላሉ። በዚያው የትምህርት ዘመን ሌሎች የስነ ምግባር ጥሰቶች ወይም የስነ ምግባር ባህሪ በሚፈጸሙበት ጊዜ፣ የትምሕርት ቤቱ ሠራተኞች **ከአስር (10)** ***ተከታታይ የትምህርት ቀናት*** ላልበለጠ ጊዜ ተመሳሳይ እርምጃ ሊወስዱ ይችላሉ። ይህ ዘዴ ተፈጻሚነት የሚኖረው ተማሪው ከመደበኛው የትምህርት ምደባ የምደባ ለውጥ እስካላስከተለ ድረስ ነው *(**በስነ ምግባር የማስጠበቅ እርምጃ ምክንያት ስለሚሆን የምደባ ለውጥ** በሚለው ርዕስ ስር ትርጓሜውን ይመልከቱ)*።

አንድ የአካል ጉዳት ያለበት ልጅ በአንድ የትምህርት ዘመን ከወቅታዊው ምደባው በድምሩ **ለአስር (10)** ***የትምህርት ቀናት*** እንዲለይ በሚረግበት ጊዜ፣ የትምህርት ዲቪዥኑን፣ በማናቸውም በዚያው የትምህርት ዓመት በሚወሰድ ቀጣይ ተመሳሳይ እርምጃ ወቅት፣ ከዚህ በማስከተል ***አገልግሎቶች*** በሚለው ርዕስ ስር የተጠቀሱትን አገልግለቶች መስጠት አለበት።

### *ተጨማሪ ሥልጣን*

የተማሪዎችን የስነ ምግባር ደንብ የጣሰው ባሕርይ የልጁ የአካል ጉዳት ነጸብራቅ ካልሆነ (ከዚህ በታች ***የመገለጫ ውሳኔ*** የሚለውን ክፍል ይመልከቱ) እና ስነ ምግባርን ለማስጠበቅ ሲባል ተግባራዊ የሚደረገው የምደባ ለውጥ ***ከአስር (10) ተከታታይ የትምህርት ቀናት*** በላይ የሆነ ጊዜ የሚወስድ ከሆነ፣ ትምህርት ቤቱ ***አገልግሎቶች*** በሚለው ክፍል የተጠቀሱትን አገልግሎቶች መስጠት ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች በሌሎች የአካል ጉዳት በሌለባቸው ልጆች ላይ በሚወስዱት እርምጃ መሠረት እና ለተመሳሳይ ጊዜ የስነ ምግባር ማስጠበቅ አሰራሮችን ተፈጻሚ ማድረግ አለባቸው። የተማሪው ወላጅ (ጆች)ን ያሚያካትት የተናጠል ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን እንዲህ ላሉት አገልግሎቶች ጊዜያዊ የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታን ይወስናል።

### *አገልግሎቶች*

> ***ልጅዎ በአንድ የትምህርት ዓመት ከ10 ቀናት በላይ የትምህርት ቤት ህግጋትን በመጣሱ ምክንያት ከትምህርት ቤት ከተባረረ እና ተግሣጽ እየተሰጣቸው ከሆነ፣ ልጅዎ የትምህርት አገልግሎት ሊሰጠው ይገባል። እንዲሁም፣ የልጅዎ ባህሪ ሊገመገም እና ባህሪው እንደገና እንዳይከሰት እቅድ ሊዘጋጅ ይችላል።***

ከወቅታዊው ምደባ ለተወገደው አካል ጉዳተኛ ልጅ መሰጠት ያለበት አገልግሎት በጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ሁኔታ ሊሰጥ ይችላል።

የትምህርት ዲቪዥኑ ከተመደበበት ቦታ ለተገለለ አካል ጉዳተኛ በዚያ የትምህርት ዘመን አገልግሎት መስጠት የሚጠበቅበት ***ለ10 የትምህርት ቀናት ወይም ከዚያ በታች*** ሲሆን ይህም ለሌሎች አካል ጉዳት ለሌባቸው ተማሪዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ከተመደቡበት ቦታ ከተገለሉ በኋላ አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ ብቻ ነው።

አካል ጉዳተኛ ልጅ አሁን ካለበት ምደባ ***ከ10 በላይ የትምህርት ቀናት*** እንዲገለል የተደረገ ተማሪ የሚከተሉት አገልግሎቶች ማግኘት አለበት፡-

1. ተማሪው በአጠቃላይ የትምህርት ስርአተ ትምህርት ውስጥ መሳተፉን እንዲቀጥል እና በልጁ የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ውስጥ የተቀመጡትን ግቦች ለማሳካት እንዲችል፣ በሌላ ሁኔታ ውስጥ ቢሆንም፣ የትምህርት አገልግሎቶችን ማግኘት፤ **እንዲሁም**
2. የባህርይ ጉድለት ያለ እንደሆነ፣ ባህርይውን ለማረቅ እና ተመልሶ እንዳይደገም አግባብነት ያለው የባህርይ ግምገማ እና የባህርይ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች እና ማስተካከያዎች ማግኘት።

የአካል ጉዳተኛ ልጅ ከወቅታዊው ምደባ በተመሳሳይ የትምህርት ዓመት **ለአስር (10) ተከታታይ የትምህርት ቀናት** እንዲገለል ከተደረገ እና ተማሪው የተገለለው **ለአስር (10) ተከታታይ ቀናት** ወይም ከዚያ በታች **ከሆነ እንዲሁም** የተማሪው እገዳ የምደባ ለውጥ ካልሆነ (ከዚህ በታች የሚገኘውን ትርጓሜ ይመልከቱ) ፣ **ቀጥሎ** የትምህርት ቤቱ ሠራተኞች ቢያንስ ከተማሪው አንድ መምህር ጋር በመነጋገር፣ ተማሪው በጠቅላላ የትምህርት ስርዓት ትምህርት ውስጥ እንዲሳተፍ እና በተማሪው የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) የተቀመጡትን ግቦች ለማሳካት የሚያስችል ምን ዓይነት አገልግሎቶች እንደሚያስፈልጉ መወሰን ይገባቸዋል፤ በእርግጥ ተማሪው በጠቅላላ የትምህርት ስርዓተ ትምህርት የሚሳተፈው በተለየ የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታ ሊሆን ይችላል።

የተማሪው መገለል የምደባ ለውጥ ከሆነ (ከስር ያለውን ትርጓሜ ይመልከቱ) የተማሪው የተናጠል ትምህርት ፕሮግራም ቡድን (IEP)፣ በሌላ የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታ ቢሆንም፣ ተማሪው በጠቅላላ ትምህርት ስርዓት ትምህርት እንዲሳተፍ እና በተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) የተቀመጡትን ግቦች እንዲያሳካ የሚያስችሉት የሚያስፈልጉ አግባብነት ያላቸውን አገልግሎቶች ላይ ውሳኔ ይሰጣል።

***የመገለጫ ውሳኔ***

| |
|---|
| ***የትምህርት ዲሲኘሉ በባህሪው ምክንያት የልጅዎን ምደባ ለመቀየር ከወሰነ፣ እርስዎ እና የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ባህሪው ከልጅዎ አካል ጉዳተኝነት ጋር የተገናኘ መሆኑን ለማወቅ መገናኘት አለብዎት። ትምህርት ቤቱም ባህሪው የተከሰተው የትምህርት ዲሲኘሉ የልጅዎን የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ባለመከተሉ እንደሆነ ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።*** |

የተማሪ የስነ ምግባር ደንብ በመጣሱ ምክንያት የአካል ጉዳተኛ ልጅን ምደባ ለመቀየር ውሳኔ ባደረጉ **በ10 የትምህርት ቀናት ውስጥ** (በተከታታይ ለ10 የትምህርት ቀናት ወይም ያነሰ ከሆነ እና የምደባ ለውጥ ካልሆነ በስተቀር) የትምህርት ዲሲኘሉ፣ ወላጅ እና የሚመለከታቸው የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን አባላት (በወላጆች እና በትምህርት ቤቱ ዲሲኘን በተወሰነው መሰረት) የሚከተሉትን ላይ ውሳኔ ለመስጠት፣ በተማሪው ፋይል ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ተዛማጅ መረጃዎች፣ የልጁን የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ፣ ማናቸውንም የመምህር ምልከታዎች እና የቀረቡ ጠቃሚ መረጃዎችን መገምገም አለባቸው።

1. የተማሪው ባህርይ በቀጥታ እና ከፍተኛ የሚባል ግንኙነት ከአካል ጉዳተኝነቱ ጋር ያለው መሆኑ ወይም በዚህ ምክንያት የመጣ ስለመሆኑ፤ ***ወይም***
2. የታየው ባህርይ የተከሰተው የትምህርት ዲሲኘሉ የተማሪው የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) በአግባቡ ተግባራዊ ባለመድረጉ ምክንያት ስለመሆኑ።

የትምህርት ዲሲኘሉ፣ ወላጅ እና የሚመለከታቸው የልጁ የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን አባላት ከእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ አንዳቸውም መሟላታቸውን ከወሰኑ፣ ባህሪው የልጁ የአካል ጉዳተኝነት መገለጫ እንደሆነ መወሰን አለበት።

የትምህርት ዲቪዥኑ፣ ወላጅ እና የሚመለከታቸው የልጁ የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን አባላት በጥያቄ ውስጥ ያለው ባህርይ የትምህርት ዲቪዥኑ የልጁ የተናጠል የትምህርት ፕሮግራምን (IEP) ተግባራዊ ባለማድረግ ቀጥተኛ ውጤት መሆኑን ከወሰኑ፣ የትምህርት ዲቪዥኑ እነዚያን ድክመቶች ለማስተካከል አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ አለበት።

### ባህርይ የልጁ የአካል ጉዳተኝነት መገለጫ መሆኑን ከተወሰነ

የትምህርት ዲቪዥኑ፣ ወላጅ እና የሚመለከታቸው የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን አባላት ድርጊቱ የልጁ የአካል ጉዳተኝነት መገለጫ መሆኑን ከወሰኑ፣ የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድኑ ከሚከተሉት አንዱን ማድረግ አለበት፡-

1. የምደባ ለውጥ ያስከተለው ባህርይ ከመከሰቱ በፊት የትምህርት ዲቪዥኑ ተግባራዊ የሆነ የባህርይ ግምገማ ካላደረገ በስተቀር፣ ተግባራዊ የሆነ የባህርይ ግምገማ ማካሄድ እና የባህርይ ጣልቃገብነት እቅድ ተግባራዊ ማድረግ፤ ወይም
2. የባህሪ ጣልቃገብነት እቅድ አስቀድሞ ከተዘጋጀ፣ ባህሪውን ለማስተካከል እንደ አስፈላጊነቱ የባህርይ ጣልቃገብነት እቅድን መከለስ እና ማሻሻል።

***በልዩ ሁኔታዎች*** በሚለው ንዑስ ርዕስ ስር እንደተገለጸው በወላጅ እና በዲቭዥኑ ስምምነት መሰረት፣ ምደባ መቀየር እንደ የስነምግባር ጣልቃገብነት እቅድ ማሻሻያ አካል ካልሆነ በስተቀር፣ የትምህርት ዲቪዥኑ ልጁን ወደ ተገለለበት ምደባ መመለስ አለበት።

### ልዩ ሁኔታዎች

**የልጅዎ ባህሪ ህገወጥ ወይም ቁጥጥር የሚደረግበት ዕጽ፣ አደገኛ መሳሪያ ወይም ከባድ የአካል ጉዳትን የሚያካትት ከሆነ፣ የትምህርት ዲቪዥኑ ልጅዎን ለመቅጣት የበለጠ ተለዋዋጭነት አለው።**

ባህሪው የልጁ የአካል ጉዳተኝነት መገለጫ ቢሆንም ባይሆንም፣ በሚከተሉት ምክኒያቶች የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ተማሪውን ወደ ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ሁኔታ (በልጁ የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን የሚወሰን) እስከ 45 የትምህርት ቀናት ድረስ ሊያገሉት ይችላሉ፡-

1. ወደ ትምህርት ቤት የጦር መሣሪያ ይዞ ከመጣ (ከዚህ በታች የተሰጠውን ትርጓሜ ይመልከቱ) ወይም በትምህርት ቤት፣ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ወይም በቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) ስር በሚገኙት የትምህርት ኤጀንሲዎች ወይም በትምህርት ዲቪዥኑ በሚተዳደር የመማሪያ ቦታ መሣሪያ ይዞ የተገኘ እንደሆነ፤
2. ሆን ብሎ ሕገወጥ ዕፅ (ከዚህ በታች የተሰጠውን ትርጓሜ ይመልከቱ) ይዞ ከተገኘ ወይም የሚጠቀም ከሆነ ወይም ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ንጥረ ነገሮች የሚሸጥ ወይም ለመሸጥ የሚፈልግ ከሆነ (ከዚህ በታች የተሰጠውን ትርጓሜ ይመልከቱ) ይህንንም የሚፈፅመው በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ፣ በቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) ስር በሚገኙት የትምህርት ኤጀንሲዎች ወይም በትምህርት ቤቱ ዲቪዥን በሚተዳደር የመማሪያ ቦታ በሚሆንበት ጊዜ፤ ወይም
3. በትምህርት ቤት፣ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ወይም በቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) ስር በሚገኙት የትምህርት ኤጀንሲዎች ወይም በትምህርት ቤቱ ዲቪዥን በሚተዳደር የመማሪያ ቦታ በሌላ ሰው ላይ ከፍተኛ የአካል ጉዳት (ትርጓሜውን ከዚህ በታች ይመልከቱ) ያስከተለ እንደሆነ።

### ትርጓሜዎች

ቁጥጥር የሚደረግበት ንጥረ ነገር ማለት ቁጥጥር በሚደረግባቸው ንጥረ ነገሮች ድንጋጌ (21 U.S.C. 812(c)) በሰንጠረዦች I፣ II፣ III፣ IV፣ ወይም V በክፍል 202(c) ስር የተካተተ መድሃኒት ወይም ሌላ ንጥረ ነገር ማለት ነው።

*ህጉ-ወጥ መድሃኒት ማለት*ቁጥጥር የሚደረግበት ንጥረ ነገር ማለት ሲሆን፤ ነገር ግን በህጋዊ መንገድ የተያዘ ወይም ፈቃድ ባለው የጤና እንክብካቤ ባለሙያ ቁጥጥር ስር ያለ ወይም በህጋዊ መንገድ የተያዘ ወይም በዚህ ድንጋጌ ወይም በሌላ በማንኛውም የፌደራል ህግ ድንጋጌ ስር ያለ ማንኛውም ባለስልጣን ቁጥጥር የሚደረግለት ንጥረ ነገርን አያካትትም።

*ከባድ የአካል ጉዳት* ትርጉሙ በዩናይትድ ስቴትስ ድንጋጌ በርዕስ 18፣ በክፍል 1365፣ በንዑስ ክፍል (h)፣ በአንቀጽ (3) ስር "ከባድ የአካል ጉዳት'' የሚለው ቃል የተሰጠውን ትርጓሜ ይይዛል። ይህ ማለት "ከፍተኛ የሆነ የሞት አደጋ፣ ከባድ የአካል ህመም፣ ረዘም ያለ እና ግልጽ የአካል ጉድለት፣ ወይም ረዘም ላለ ጊዜ የአካል፣ የአካል ክፍል ወይም የአዕምሮ ፋኩልቲ ተግባር ማጣት ወይም እክልን የሚያካትት የአካል ጉዳት'' ማለት ነው።

*የጦር መሣሪያ* በዩናይትድ ስቴትስ ድንጋጌ በርእስ 18፣ ክፍል 930፣ አንቀጽ (2) ንዑስ ክፍል (g) እና *በቨርጂኒያ ድንጋጌ* አንቀጽ 18.2-308.1 ስር ለ"አደገኛ የጦር መሳሪያ" የተሰጠውን ትርጓሜ ይይዛል። አደገኛ የጦር መሳሪያ ማለት እንደ መሳሪያ፣ መገልገያ እቃ፣ ቁሳቁስ ወይም ንጥረ ነገር፣ ህይወት ያለው ወይም ግዑዝ፣ ለሞት የሚዳርግ ወይም ከባድ የአካል ጉዳት በቀላሉ ሊያደርስ የሚችል ወይም የሚያገለግል የሚችል ማለት ነው፣ ይህ ቃል ሹል የሆነ ከ3 ኢንች ያነሰ ርዝመት ያለው የኪስ ቢላን አያካትትም።

### ማስታወቂያ

**የትምህርት ዲቪዥኑ የተማሪዎች የስነ ምግባር ደንብ በመጣሱ ምክንያት የልጅዎን ምደባ ለመቀየር ወሳኔ በሰጠበት ቀን ይህንን ውሳኔ ለእርስዎ ማሳወቅ እና የአሰራር ከለላዎች (ፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ) ማሳወቂያ ሊሰጥዎ ይገባል።**

### በስነ ምግባር ጉድለት ምክንያት ስለሚደረግ የምደባ ለውጥ

**የልጅዎ ከትምህርት ቤት መታገድ በአንዳንድ ሁኔታዎች እንደ "የምደባ ለውጥ" ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።**

የአንድ አካል ጉዳተኛ ልጅ፣ ከልጁ የትምህርት ምደባ መገለል እንደ **የምደባ ለውጥ** የሚሆንበት:-

1. መገለሉ ለተከታታይ 10 የትምህርት ቀናት በላይ ሲሆን፤ <u>**ወይም**</u>
2. ከዚህ በሚከተሉት ምክንያቶች፣ ልጅዎ በተደጋጋሚ እንዲገለል ተደርጎ ከሆኑ:-
   ሀ. በአንድ የትምህርት ዓመት በአጠቃላይ ከ10 የትምህርት ቀናት በላይ ተከታታይ መገለሎች
   ለ. የልጅዎ ባህርይ በተደጋጋሚ ለመገለል ምክኒያት ከሆነበት ባህርይ ጋር እጅጉን ተመሳሳይ ከሆነ፤ <u>**እና**</u>
   ሐ. ሌሎች ተጨማሪ ነገሮች እንደ ልጅዎ ተገሎ የቆየበት የጊዜ ርዝመት፣ ልጅዎ በዚህ መልኩ የቆየበት ጠቅላላ ጊዜ እና እንዲህ ዓይነት እርምጃዎች የሚወሰዱት በቅርብ ድግግሞች ከሆነ፤

የማግለያው ዘዴ የምደባ ለውጥ እንደሚያካትት እንደየ ሁኔታው በትምህርት ዲቪዥኑ የሚወሰን ቢሆንም፣ ተቃውሞ ካጋጠመው ግን በፍትህ ሂደት እና በዳኝነት ችሎት ሊገመገም ይችላል።

### የጊዜያዊ የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታን ውሳኔ

የተናጠል ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን፣ ***የምደባ ለውጥ*** ሲደረግ እና ***ተጨማሪ ስልጣን*** እና ***ልዩ ሁኔታዎች*** በሚሉት ክፍሎች መሰረት ተማሪዎች ሲገለሉ ጊዜያዊ የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታን መወሰን አለበት።

**ልጅዎ በሚቀጣበት ጊዜ በትምህርት ዲቪዥኑ ውሳኔ ካልተስማሙ፣ ለፍትህ ሂደት ችሎት የመጠየቅ መብት አልዎት።**

**አጠቃላይ**

የአካል ጉዳተኛው ልጅ ወላጅ በሚከተሉት ላይ ካልተስማማ የፍትህ ሂደት (ከላይ ያለውን ይመልከቱ) ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡-

1. በእነዚህ የስነ ምግባር ማስጠበቂያ ድንጋጌዎች ውስጥ የተደረገ ምደባን በተመለከተ ማንኛውም ውሳኔ፤ **ወይም**
2. ከላይ የተገለፀው የመገለጫ ውሳኔ

የትምህርት ዲቪዥኑ ልጁን በወቅታዊ ምደባው ማቆየት በልጁ ወይም በሌሎች ላይ ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል ካመነ፣ የፍትህ ሂደት ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል።

**የችሎት ሹም ስልጣን**

***የማያዳላ የችሎት ሹም*** በሚል ንዑስ ርዕስ ስር የተገለጹትን መስፈርቶች የሚያሟላ የችሎት ሹም የፍትህ ሂደቱን ችሎት ማካሄድ እና ውሳኔ መስጠት አለበት። የችሎት ሹሙ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላል፡-

1. የችሎቱ ሹም መገለሉ ***በትምህርት ቤት ሰራተኞች ስልጣን*** ስር የተገለጹትን መስፈርቶች መጣሱን ወይም የልጁ ባህሪ የአካል ጉዳተኝነት መገለጫ መሆኑን ከወሰነ፣አካለ ጉዳተኛው ልጅ ወደ ተወገደበት ምደባ መመለስ፤ ወይም

2. የችሎቱ ሹም ልጁን በወቅታዊ ምደባው ማቆየት በልጁ ላይ ወይም በሌሎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል ከወሰነ፣ አካል ጉዳተኛ ልጁን ወደ ተገቢ ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ሁኔታ ከ45 የትምህርት ቀናት ላልበለጠ እንዲቀየር ማዘዝ።

የትምህርት ዲቪዥኑ ልጁን ወደ መጀመሪያው ምድብ መመለስ በልጁ ወይም በሌሎች ላይ ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል ካመነ፣ እነዚህ የችሎት ሂደቶች ሊደገሙ ይችላሉ።

በማንኛውም ጊዜ ወላጅ ወይም የትምህርት ዲቪዥኑ የፍትህ ሂደት ጥያቄን የሚመለከት ችሎት ሲጠይቁ ፣ከሚከተሉት ሁኔታዎች በስተቀር፣***ለፍትህ ሂደት ጥያቄ ማቅረብ ፣ የፍትህ ሂደት ጥያቄ ችሎቶች*** በሚለው ርዕስ ስር የተገለጹትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው።

1. የትምህርት ዲቭዥኑ ችሎቱ ከተጠየቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት ***ሃያ*** **(20)** የትምህርት ቀናት ውስጥ የተፋጠነ የፍትህ ሂደት ችሎት ማዘጋጀት ይኖርበታል እና ችሎቱ ከተካሄደ በኋላ ባሉት **አስር 10** የትምህርት ቀናት ውስጥ ውሳኔ መገኘት አለበት፤
2. እርስዎ እና የትምህርት ዲቪዥኑ ስብሰባውን እንዲቀር በጽሁፍ ካልተስማማችሁ ወይም ሽምግልና ለመጠቀም ካልተስማማችሁ በስተቀር፣ የመፍትሄ ስብሰባው የፍትህ ሂደት ጥያቄው በደረሰ **በሰባት (7)** ተከታታይ ቀናት ውስጥ መካሄድ አለበት። የፍትህ ሂደት ጥያቄው በደረሰ **በአስራ አምስት (15)** ተከታታይ ቀናት ውስጥ ለሁለቱም ወገኖች አመርቂ በሆነ ሁኔታ ጉዳዩ ካልተፈታ በስተቀር፣ የፍትህ ሂደት ችሎቱ ሊቀጥል ይችላል።

ማንኛውም አካል፣ እንደማናቸውም ሌሎች የፍትህ ሂደት ችሎት ውሳኔዎች ሁሉ በዚህ በተፋጠነ የችሎት ሂደት የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ማለት ይችላል (ከላይ **ይግባኝ** የሚለውን ርዕስ ይመልከቱ)።

## በይግባኝ ወቅት ስለሚኖር ምደባ

ከላይ እንደተገለፀው፣ ወላጅ ወይም የትምህርት ዲቪዥኑ፣ ከስነ ምግባር ጉዳዮች ጋር በተገናኘ የፍትህ ሂደት እንዲደረግ ጥያቄ ሲያቀርቡ፣ የችሎቱ ሹም ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ወይም ***በትምህርት ቤት ሰራተኞች* ስልጣን** በሚለው ርዕስ ስር በተደነገገው እና በተገለፀው መሰረት የተገለለበት ጊዜ እስኪያበቃ ድረስ፣ በየትኛውም ቀድም የተከሰተውን በመከተል፣ ልጁ በጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ሁኔታ ውስጥ መቆየት አለበት (ወላጅ እና የትምህርት ዲቪዥኑ በተቃራኒው ካልተስማሙ በስተቀር)።

## ለልዩ ትምህርት እና ተያያዥ ለሆኑ አገልግሎቶች ለጊዜው ብቁ ላልሆኑ ልጆች ስለሚደረግ ጥበቃ

**የልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ገና ለማያገኝ ልጅዎ፣ ከስነ ምግባር በተያያዙ እርምጃዎች ላይ አንዳንድ ጥበቃዎችን የመጠበቅ መብት አልዎት።**

### አጠቃላይ

የልጅዎ ለልዩ ትምህርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች ብቁነቱ ገና ካልተወሰነ እና ልጅዎ የትምህርት ቤት የተማሪዎች ስነ ምግባር ደንብን የጣሰ እንደሆነ ነገር ግን የትምህርት ዲቪዥኑ (ከዚህ በታች እንደተወሰነው) የስነ ምግባር እርምጃ እንዲወሰድ ያደረገው ባህርይ ከመከሰቱ በፊት ልጅዎ አካል ጉዳተኛ መሆኑን ያውቅ ከነበረ፣ ልጅዎ በዚህ ማሳወቂያ የተገለፁትን ማናቸውንም ጥበቃዎች ሊጠይቅ ትችላለች።

### የስነ ስርዓት ጉዳዮች ግንዛቤ ምንጭ

ከዚህ በሚከተሉት ሁኔታዎች የትምህርት ዲቪዥኑ የስነ ምግባር እርምጃ እንዲወሰድ ያደረገው ባህርይ ከመከሰቱ በፊት ልጅዎ የአካል ጉዳተኝነት እንዳለበት ያውቅ ነበር ተብሎ ሊወሰድ ይችላሉ፡-

1. የልጁ ወላጅ ለተቆጣጣሪ ወይም አግባብነት ላለው የትምህርት ኤጀንሲ የአስተዳደር ሠራተኞች ወይም ለልጅዎ መምህር፣ ልጃቸው የልዩ ትምህርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች ሳያስፈልገው አይቀርም ብለው እንደሚያምኑ ስጋታቸውን በጽሁፍ ካሳወቁ፤
2. ወላጁ በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ክፍል B መሠረት ለልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ብቁነት ጋር የተያያዘ ግምገማ ጠይቀው ከነበረ፤ ***ወይም***
3. የልጅዎ መምህር ወይም ሌሎች የትምህርት ዲቪዥኑ ሠራተኞች ልጅዎ ስለሚያሳየው ተከታታይ ባህርይ የሚያሳስባቸው ግልፅ የሆነ ነገር እንዳለ ለትምህርት ዲቪዥኑ የልዩ ትምህርት ዳይሬክተር ወይም የትምህርት ዲቪዥኑ ሰራተኞች ተቆጣጣሪ ስጋታቸው የገለፁ እንደሆነ።

### ልዩ ሁኔታ

ከዚህ በሚከተሉት ሁኔታዎች የትምህርት ዲቪዥኑ ከላይ የተገለጹትን ያውቅ ነበር ለማለት ተብሎ ሊወሰድ አይቻልም፡-

1. የልጁ ወላጅ ለልጁ ግምገማ እንዲካሄድበት ወይም የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች እንዲሰጠው ፈቃደኛ ካልሆኑ፤ ***ወይም***
2. ልጁ ተገምግሞ እና በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ስር አካል ጉዳተኛ ልጅ እንዳልሆነ ተወስኖ ከሆነ።

### *መሠረታዊ ግንዛቤ በሌለበት ሁኔታ ተፈጻሚ የሚሆኑ ሁኔታዎች*

በልጅዎ ላይ የስነ ምግባር እርምጃዎች ከመውሰድ በፊት የትምህርት ዲቪዥኑ፣ ከላይ ***የስነ ስርዓት ጉዳዮች ግንዛቤ ምንጭ* እና *የተለየ ሁኔታ*** በሚሉት ንዑስ ክፍሎች ስር እንደተብራራው፣ ስለ ልጅዎ የአካል ጉዳተኝነት ግንዛቤ ካልነበረው፣

ልጅዎ የአካል ጉዳተኝነት ለሌላቸው ተመጣጣኝ የሆነ ባህርይ በሚያሳዩ ልጆች ላይ ተፈጻሚ የሚደረጉ የስነ ምግባር እርምጃዎች ሊወሰዱበት ይችላሉ። ሆኖም ግን፣ ልጅዎ የስነ ምግባር እርምጃ ተወስዶበት ባለበት ጊዜ ውስጥ ግምገማ እንዲካሄድ ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ፣ እንዲህ ያለው ግምገማ በአፋጣኝ መካሄድ አለበት።

ግምገማው እስኪጠናቀቅ ድረስ ልጁ በትምህርት ቤት ባለስልጣናት በተደነገገው የትምህርት ምደባ ውስጥ ይቆያል፤ ይህም ያለትምህርት አገልግሎት መታገድን ወይም መባረርን ይጨምራል።

ልጁ አካል ጉዳተኛ ነው ተብሎ ከተወሰነ፣ በትምህርት ዲቪዥኑ ከተካሄደው ግምገማ እና በወላጆች የተሰጠውን መረጃ ከግምት ውስጥ በማስገባት የትምህርት ቤቱ ዲቪዥን፣ በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) መሠረት ከላይ የተገለጹትን የተግሳጽ መስፈርቶችን ጨምሮ የልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን መስጠት አለበት።

### ጉዳዩን ለሕግ አስከባሪ እና ለፍርድ ቤት አካላት መላክ እና በእነርሱ የሚወሰዱ እርምጃዎች

**በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ ፖሊስ ወይም ፍርድ ቤቶች ከልጅዎ የትምህርት ዲቪዥኑ ስለ ልጅዎ መረጃ ሊያገኙ ይችላሉ።**

የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ክፍል B፣ የሚከተሉትን አያደርግም:-

1. አንድን ኤጀንሲ አካል ጉዳተኛ ልጅ የፈፀመውን ወንጀል ለሚመለከታቸው ባለስልጣናት ሪፖርት እንዳያደርግ መከልከል፤ <u>ወይም</u>

2. የቨርጂኒያ ህግ አስከባሪ እና የፍትህ ባለስልጣናት የፌደራል እና የስቴት ህግ አካል ጉዳተኛ ልጅ ለሚፈጽሟቸው ወንጀሎች አተገባበርን በተመለከተ ኃላፊነታቸውን እንዳይወጡ መከልከል።

**መዝገቦችን ስለማስተላለፍ**

አንድ የትምህርት ዲቪዥን አካል ጉዳተኛ ልጅ የፈፀመውን ወንጀል ሪፖርት ካደረገ፣ የትምህርት ዲቪዥኑ:-

1. የልጁ የልዩ ትምህርት እና የስነ ምግባር መዛግብት ቅጂዎች ሪፖርቱን በሚያቀርቡላቸው የኤጀንሲ ኃላፊዎች እንዲታዩ ቅጂዎቻቸው ለእነርሱ መድረሱን ማረጋገጥ አለበት፤ <u>እና</u>
2. የቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና ግላዊነት ድንጋጌ (FERPA) በሚፈቅደው ልክ ብቻ የልጁን የልዩ ትምህርት እና የስነ ምግባር መዛግብት ቅጂዎችን ማስተላለፍ ይችላል።

## በሕዝብ ወጪ ልጆችን በራሳቸው ውሳኔ በግል ትምህርት ቤቶች ለማስገባት ተፈጻሚነት ያላቸው መስፈርቶች

### አጠቃላይ

**ልጅዎን በራስዎት ፈቃድ በግል ትምህርት ቤት ሲያስመዘግቡ፣ የተወሰኑ አገልግሎቶችን የማግኘት መብት ሊኖርዎት ይችላል።**

የትምህርት ዲቪዥኑ ለልጅዎ ነጻ እና ተገቢ የህዝብ ትምህርት (FAPE) የሚያገኙበትን ዕድል አመቻችቶ እያለ እርስዎ በራስዎ ፍላጐት በአንድ የግል ትምህርት ቤት ወይም ተቋም ለማስገባት ከወሰኑ፣ የትምህርት ዲቪዥኑ የልዩ ትምህርት እና ተያያዥ አገልግሎቶችን ጨምሮ ለእነዚህ የሚያስፈልገውን ወጪ እንዲሸፍን በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ክፍል B አያስገድደውም። ነገር ግን፣ የግል ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት የትምህርት ዲቪዥን ልጅዎን በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) አገልግሎቶች መሠረት በ34 CFR §§300.131 እስከ 300.144 ስር በወላጆቻቸው በግል ትምህርት ቤት የተመዘገቡ ልጆችን በሚመለከት ስር ፍላጐቶቻቸው ሊሟሉላቸው ከሚገባ ልጆች ጋር ማካተት አለበት።

**ለግል ትምህርት ቤት የሚፈፀምን ክፍያ ስለማካካስ**

ልጅዎ ቀደም ሲል የልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች በትምህርት ዲቪዥን ያገኘ የነበረ እንደሆነ እና ልጅዎን በግል የቅድመ ልጅነት ትምህርት ቤት፣ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ያለ የትምህርት ዲቪዥኑ ፈቃድ ወይም ሪፈራል ባላደረገበት ሁኔታ ያስገቡ እንደሆነ፣ ፍርድ ቤት ወይም የችሎት ሹሙ ይህ ኤጀንሲ በግል ትምህርት ቤቱ ያወጡትን ወጪ ተመላሽ እንዲያደርግልዎ ኤጀንሲውን ሊያዙ ይችላሉ፤ ይህ የሚሆነው ፍርድ ቤቱ ወይም የችሎት ሹሙ ልጅዎ በተገለፀው ተቋም ከመግባቱ በፊት የትምህርት ዲቪዥኑ ነጻ እና አግባብነት ያለው የህዝብ ትምህርት (FAPE) እድልን በጊዜው አላመቻቸም የሚል ውሳኔ ከሰጡ እና በግል ትምህርት ቤት መግባቱ አግባብነት አለው ብሎ ሲወስን ነው። ምንም እንኳን ምደባው በቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) እና በትምህርት ዲቪዥኖች የሚሰጠውን ትምህርት የሚመለከቱትን የቨርጂኒያ መመዘኛዎችን ባያሟላም፣ የችሎት ሹሙ ወይም ፍርድ ቤት ምደባዎ ተገቢ ሆኖ ሊያገኘው ይችላል።

**ወጪ በማካካስ ላይ ተፈጻሚነት ያለው ገደብ**

ከላይ ባለው አንቀጽ ላይ የተገለፀው የወጪ ማካካሻ ሊቀንስ ወይም ሊከለከል ይችላል፡-

1. (ሀ) ልጅዎን ከህዝብ ትምህርት ቤት ከማስወጣትዎ በፊት በተሳተፉበት በጣም የቅርብ ጊዜ የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ስብሰባ፣ ለልጅዎ ነጻ እና ተገቢ የህዝብ ትምህርት (FAPE) እንዲያቀርቡ በትምህርት ዲቪዥኑ የቀረበውን ምደባ እንደማይቀበሉ ለተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን ካላሳወቁ፣ ስጋቶችዎን እና ልጅዎን በህዝብ ወጪ በግል ትምህርት ቤት የማስመዝገብ ፍላጎትዎን ጨምሮ ካልገለጹ፣ ወይም (ለ) ልጅዎን ከህዝብ ትምህርት ቤት ከማስወጣትዎ በፊት ቢያንስ 10 የሥራ ቀናት (በሥራ ቀን የሚዉሉ ማንኛውም በዓላትን ጨምሮ)፣ መረጃውን ለትምህርት ዲቪዥኑ የጽሁፍ ማሳሰቢያ ያልሰጡ ከሆነ፤

2. ልጅዎን ከህዝብ ትምህርት ቤት ከማስወጣትዎ በፊት የትምህርት ዲቪዥኑ ልጅዎን ለመገምገም ያለውን ፍላጎት (የግምገማውን አላማ ተገቢ እና ምክንያታዊ የሆነውን መግለጫን ጨምሮ) አስቀድሞ የጽሁፍ ማሳወቂያ ከሰጠዎት እርስዎ ግን ልጁ ለግምገማው ላይ እንዲገኝ ካላደረጉ፤ **ወይም**

3. ፍርድ ቤት የእርስዎ ተግባራት ምክንያታዊነት የጐደላቸው ናቸው የሚል ውሳኔ ከወሰነ።

ሆኖም ግን ተመላሽ የሚደረገው የማካካሻ ወጪ፡-

1. ከዚህ በሚከተሉት ሁኔታዎች ማሳወቂያ አልተሰጠም በሚል ምክንያት ላይቀነስ ወይም ውድቅ ላይደረግ ይችላል፡- (ሀ) ትምህርት ቤቱ ማሳወቂያውን እንዳይሰጡ ከከለከልዎት፤ (ለ) ከዚህ በላይ የተገለጸውን ማሳወቂያ የማቅረብ ኃላፊነት እንዳለብዎት ማሳወቂያ አልደረሰዎትም፤ ወይም (ሐ) ከላይ የተገለፁትን መስፈርቶች ተቀብለው ቢያሟሉ በልጅዎ ላይ ከፍተኛ አካላዊ ጉዳት የሚያስከተል ከሆነ፤ **እና**
2. በፍርድ ቤት ወይም በችሎት ሹም ውሳኔ መሰረት ወላጆቹ አስፈላጊውን ማሳወቂያ ባለማቅረባቸው ምክንያት ላይቀነስ ወይም ላይከለከል ይችላል፡- (ሀ) ወላጁ ማንበብና መጻፍ የማይችል ወይም በእንግሊዝኛ መጻፍ የማይችል ከሆነ፤ ወይም (ለ) ከላይ የተገለፁትን መስፈርቶች ተቀብለው ቢያሟሉ በልጁ ላይ ከፍተኛ የስነ ልቦና ጉዳት የሚያስከትል ከሆነ።

## የህዝብ ጥቅሞችን ወይም ኢንሹራንስ አጠቃቀምን በተመለከተ የወላጅ መብቶች ማሳወቂያ

***የትምህርት ቤቱ ዲቪዥን ማንኛውንም የህዝብ ወይም የግል ጥቅማጥቅሞችን ወይም ኢንሹራንስን ከመጠቀምዎ በፊት የጽሁፍ ፈቃድዎን ማግኘት እና ከህዝባዊ ጥቅማጥቅሞች ወይም ኢንሹራንስ አጠቃቀም ጋር በተገናኘ ስለመብትዎ አመታዊ ማሳሰቢያ መስጠት አለበት።***

የአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲዎች፣ ሜዲኬይድን ወይም ሌላ ህዝባዊ ጥቅማ ጥቅሞችን ወይም የመድን ፕሮግራሞችን ለመጠቀም በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ክፍል B ስር የሚፈለጉትን አገልግሎቶች ለማቅረብ ወይም ለመክፈል አንድ ልጅ የሚሳተፍባቸውን የኢንሹራንስ ፕሮግራሞች በህዝባዊ ጥቅማጥቅሞች ወይም የኢንሹራንስ መርሃ ግብሮች መሰረት በተፈቀደው መሰረት ሊጠይቁ ይችላሉ። የህዝብ ኤጀንሲዎች የልጁን ወይም የወላጆችን የህዝብ ጥቅማ ጥቅሞችን ወይም ኢንሹራንስን ለመጀመሪያ ጊዜ ከማግኘታቸው በፊት የአንድ ጊዜ የወላጅ ፈቃድ እንዲያገኙ በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ይጠይቃል። የአንድ ጊዜ የወላጅ ስምምነት የሚከተሉትን መግለጽ አለበት፡-

1. ይፋ ሊደረግ የሚችለው የግል ማንነት ሊገልጽ የሚችል መረጃ፤
2. የይፋ መደረጉ ዓላማ፤
3. ይፋ ሊደረግለት የሚችል ኤጀንሲ፤
4. የህዝብ ድርጅቱ በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ክፍል B ስር ለሚሰጡ አገልግሎቶችን ለመክፈል የወላጅ ወይም የልጁን የህዝብ ጥቅማጥቅሞች ወይም መድን መረጃ ማግኘት እንደሚችል ወላጁ ተረድቶ ይስማማል።

የአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲዎች የልጁን ወይም የወላጆችን የህዝብ መድን መረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ ከማግኘታቸው በፊት፣ የአንድ ጊዜ የወላጅ ስምምነት ከማግኘታቸው በፊት እና ከዚያ በኋላ በየዓመቱ ለልጁ ወላጅ የጽሁፍ ማሳወቂያ መስጠት አለባቸው።

ወላጆች በማንኛውም ጊዜ የልጃቸውን የግል ማንነት ሊገልጹ የሚችሉ መረጃ ለስቴቱ የህዝብ ጥቅማጥቅሞች ወይም የኢንሹራንስ ፕሮግራም አስተዳደር ኃላፊነት ላለው ኤጀንሲ ለማሳወቅ ፈቃዳቸውን የመሰረዝ መብት አላቸው። ፈቃድን መሻር ወይም የግል ማንነት ሊገልጹ የሚችሉ መረጃ ይፋ ለማድረግ ፈቃድ አለመስጠት የህዝብ ድርጅቱን ሁሉንም አስፈላጊ አገልግሎቶች ያለምንም ወጪ መሰጠቱን የማረጋገጥ ሀላፊነቱን አይገድበውም።

የአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲዎች፡-

1. በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA) ክፍል B መሠረት ልጃቸው FAPE እንዲያገኝ ወላጆች በሕዝብ ጥቅማ ጥቅሞች ወይም የኢንሹራንስ ፕሮግራሞች እንዲመዘገቡ አይጠይቅም።

2. ወላጆች በዚህ ክፍል መሠረት ለሚሰጡ አገልግሎቶች የይገባኛል ጥያቄ ለማቅረብ እንደ ተቀናሽ ወይም የጋራ ክፍያ መጠን ለመክፈል፣ ከኪስ የሚከፈሉ ወጪዎችን ለመክፈል ላያስገድዳቸው ቢችልም የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ ወላጆች ሊከፍሉት የሚገባቸውን ወጪ ሊከፍል ይችላል።

3. ኤጀንሲው የልጁን ጥቅማ ጥቅሞችን በህዝባዊ ጥቅማጥቅሞች ወይም በኢንሹራንስ ፕሮግራም መጠቀም የማይችለው የሚከተለው ችግሮችን የሚያስከትል ሲሆን ነው፤

   ሀ. ያለውን የዕድሜ ልክ ሽፋን ወይም ሌላ ማንኛውንም የመድን ሽፋን ጥቅማጥቅሞችን መቀነስ፤
   ለ. በሕዝብ ጥቅማጥቅሞች ወይም በኢንሹራንስ መርሃ ግብር የሚሸፈኑ የነበሩ እና ልጁ ትምህርት ቤት ከሚያሳልፍበት ጊዜ ውጪ ለልጁ አስፈላጊ ለሆኑ አገልግሎቶች ቤተሰቡን ወጪ ካስወጣ፤
   ሐ. የክፍያን መጨመር ወይም ጥቅማጥቅሞች ወይም ኢንሹራንስ መቋረጥን የሚያስከትል ከሆነ፤ ወይም
   መ. በአጠቃላይ ከጤና ጋር በተያያዙ ወጪዎች ላይ በመመስረት ለቤት እና ለማህበረሰብ-ተኮር ብቁነትን የማጣት አደጋ የሚያጋልጥ ከሆነ።